# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት



## በኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን
## የዱር እንሰሳት ልማት፤ጥበቃ እና አጠቃቀም
## በተመለከተ የተከናወነ የአካባቢ ኦዲት ረቂቅ ሪፖርት

ሰኔ 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ


ክፍል አንድ ....1

መግቢያ ....1

የባለስልጣኑ ዓላማ፤ ሥልጣንና ተግባር ; ....3

የባለስልጣኑ አደረጃጀትና የሰው ሀይል ....5

የባለስልጣኑ የፋይናንስ ምንጭ ....5

የኦዲቱ አላማ ....5

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች እና መመዘኛዎች (AUDIT ISSUES AND EVALUATIVE CRITERIA) ....6

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ....6

የሥራ ሂደት መግለጫ (PROCESS DESCRIPTION) ....8

ክፍል ሁለት ....10

የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ስርዓት አስተዳደር መኖሩን ተግባራዊ መደረጉንና ውጤታማነቱን በተመለከተ ....10

በሀገሪቱ የሚገኙ የዱር እንስሳት ዓይነት፤ብዛትና ሥርጭት ጥናት ስለመከናወኑ እና የጥበቃ ቦታዎች ህጋዊ ሰውነት ማግኘታቸውን በተመለከተ ....10

ለዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች የፓርክ ማኔጅመንት ዕቅድ(PARK MANAGEMENT PLAN) መዘጋጀቱን በተመለከተ ....12

በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ ህገ-ወጥ ተግባራት መከናወን/ አለመከናወናቸውን በተመለከተ ....13

በዱር አንስሳት የጥበቃ ቦታዎች ውስጥና አካባቢ የልማት እንቅስቃሴዎች ከመከናወኑ በፊት አካባቢያዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት መካሄዱን በተመለከተ ....17

በሀገራችን ብቻ ለሚገኙና ለእልቂት ስጋት ለተጋለጡ የዱር እንስሳት ጥበቃ እንዲደረግላቸው የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ ....19

ከጥበቃ ቦታዎች ውጭ ያሉት የዱር እንስሳት የሚጠበቁበትና የመኖሪያ አካባቢያቸው የሚተዳደሩበት ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ ....20

በዱር እንስሳት ላይ የሚደርሱትን የተፈጥሮና የሰው ሰራሽ አደጋዎችን አስቀድሞ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ ....21

የዱር እንስሳት በሰውና አካባቢያቸው ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ለማድረግ የቅድመ-መከላከል ሥርዓት መኖሩን በተመለከተ ....23

በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ ሰው ሰራሽ እና ተፈጥሮአዊ ለውጦች ክትትል /ECOLOGICAL MONITORING/ መኖሩን በተመለከተ ....24

የዱር እንስሳት ሀብት ላይ የተመሰረተ ቱሪዝም ልማት እንቅስቃሴዎች መኖራቸው፤ ተግባራዊ መደረጋቸውንና ውጤታማ መሆናቸውን መገምገምን በተመለከተ ....27

በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የተዘረጉ የመሰረተ-ልማት አውታሮችን በተመለከተ ....27

በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ ለሚከናወኑ የቱሪዝም እንቅስቃሴዎች አጋዥ የሆኑ ምልክቶች መኖራቸውን በተመለከተ ..... 28

የጥበቃ ቦታዎች በአካባቢው የሚገኘውን ሕብረተሰብ ተጠቃሚ የቱሪዝም መስህብ የያዘ የቱሪስት ፓኬጅ ስለመዘጋጀቱ ..... 29

በዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎችን ለማገዝ የሚወጡ መመሪያዎችን በተመለከተ ..... 31

በፍጆታዊ መልኩ/ CONSUMPTIVE / የዱር እንስሳት ሀብት አጠቃቀምን በተመለከተ ..... 32

የዱር እንስሳትና የውጤቶቻቸው ዝውውር ለመቆጣጠር የተዘረጋውን ሥርዓት በተመለከተ ..... 33

በአገሪቱ ያለውን የዱር እንስሳት ክምችት ለማወቅ፣ለመጠበቅና የዘለቄታዊ አጠቃቀም ስልት ለመቀየስ የሚረዳ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ መኖሩን፣ተግባራዊ መደረጉንና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ ..... 37

በባለድርሻ አካላት መካከል የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ለመፍጠር የሚያስችል ስርዓት ስለመዘርጋቱ ..... 37

በሀገሪቱ ስለሚገኙ የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች ዝርዝር መረጃና የተካሄዱ ጥናቶችን በተመለከተ ..... 38

የጥበቃ ቦታዎችን ማራኪ ገፅታና የዱር እንስሳትና ውጤቶቻቸውን የማስተዋወቅ ስራን በተመለከተ ..... 39

ስለዱር እንስሳትና የጥበቃ ቦታዎች የሚደረገውን የግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ በተመለከተ ..... 40

በጥበቃ ቦታዎች መካከል የሚደረግ የልምድ ልውውጥ በተመለከተ ..... 40

ክፍል ሦስት ..... 42

መደምደሚያዎች ..... 42

ክፍል አራት ..... 45

የማሻሻያ ሃሳቦች ..... 45

አባሪ 1 ..... 50

አባሪ 2 ..... 53

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. ኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ዓይነት የተፈጥሮ ውበት ያላቸውን ብርቅ የሆኑ የዱር እንስሳት ዝርያዎች ባለቤት ነች፡፡ ከእነዚህ ውስጥ በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚገኙ ብርቅዬ እንስሳትና አዕዋፋት ይገኙበታል፡፡ እስካሁን በተደረጉ ጥናቶች መሰረት በሀገራችን ከ2786 በላይ የተለያዩ የዱር እንስሳት ዝርያዎች እንደሚገኙ የታወቀ ሲሆን፣ ከእነርሱም መካከል 203 ያህሉ በሀገራችን ብቻ የሚገኙ /ENDEMIC SPECIES/ ናቸው፡፡ እንዲሁም ከ7000 በላይ የተለያዩ "ከፍተኛ" የእፅዋት ዝርያዎች /HIGHER PLANT SPECIES / ያሉና ከ10-12% የሚሆኑት በሀገራችን ብቻ የሚገኙ ናቸው፡፡ ይህ ሀብቷ በሀገሪቱ የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ጉልህ አስተዋፅኦ የሚያደርግ እምቅ የተፈጥሮ ሀብት ቢሆንም ከንዑስ-ክፍለ ኢኮኖሚው እስከ አሁን ድረስ የሚጠበቀውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ሳታገኝ ቆይታለች፡፡

2. ለዚህም ዋና ዋና ምክንያቶች ሆነው ከሚጠቀሱት መካከል፤ አግባብነት በሌለው የመሬት አጠቃቀም መንስኤ በዱር እንስሳትና በመኖሪያ አካባቢያቸው ላይ የሚደርሰው ውድመት፤ ያልተመጣጠነ የሕዝብ ብዛት ዕድገት የሚፈጥረው ጫናና የሕገ-ወጥ ሰፈራ መስፋፋት፤ የሕገ-ወጥ አደን ዋና ዋናዎቹ ምክንያቶች ናቸው፡፡ ከዚህም የተነሳ የዱር እንስሳቱ እጅግ ለከፋ አደጋ ተጋልጠው ይገኛሉ፡፡

3. በሀገሪቱ የዱር እንስሳት ሀብት ላይ እየተባባሰ የመጣውን የእልቂት ብሎም የመጥፋትን አደጋ በአፋጣኝ መግታት አለበት፡፡ ይህንንም በማድረግ አገሪቱ ከዚህ የዱር እንስሳት ሀብት፤ በሕይወት፣ በውጤቶቻቸው ንግድ፣ በስፖርታዊ አደንና በመሳሰሉት ከቱሪዝም ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማግኘት ትችላለች፡፡ ይህንን ለማድረግ ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታና አሁን ካለው ዓለም አቀፍ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ መርህ አኳያ የተቃኘ የዱር እንስሳት ልማት፣ አጠቃቀም እና ጥበቃን የሚያሳይ አቅጣጫ መንደፍ ትኩረት የሚሰጠው አብይ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ፖሊሲና ስትራቴጂ በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሰኔ 2001 ተዘጋጅቷል፡፡

### የባለስልጣን መ/ቤቱ ታሪካዊ አመጣጥ

4. በኢትዮጵያ ውስጥ የዱር እንስሳት ጥበቃን በተመለከተ የመጀመሪያው ሕግ የወጣው በአፄ ምኒሊክ ዘመነ መንግስት ነው፡፡ ዳግማዊ ምኒልክ በጥምቅት 6/1901 ዓ.ም. ዘጠኝ አንቀፅ የያዘና በዕድሜ ትንሽ የሆኑ ዝሆኖች እንዳይታደኑ የሚከለክል ደንብ አወጡ፡፡ ይህም ደንብ

የጥርሳቸው ክብደት ከ17 ኪ.ግ በታች የሆኑ ዝሆኖች እንዳይታደኑ ይከለክል ነበር፡፡ የአንድ ትልቅ ዝሆን ጥርስ በአማካይ ከ20-45 ኪ.ግ ስለሚመዝን በደንቡ ላይ የተቀመጠው የዝሆን ጥርስ ክብደት ትንንሽ ዝሆኖች እንዲጠበቁ ረድቷል፡፡

5. የዱር እንስሳት ጥበቃን በሚመለከት የመጀመሪያው አዋጅ የወጣው ግንቦት 21 ቀን 1936 ዓ.ም. ነው፡፡ በቀጣይም የዚህ አዋጅ ማስፈፀሚያ ደንብ በ1937 ዓ.ም. በእርሻ ሚኒስቴር ወጣ፡፡ በዩኔስኮ ልኡካን ቡድን በ1957ዓ.ም. የዱር እንስሳትን የሚያለማና የሚጠብቅ ተቋም እንዲቋቋም ለኢትዮጵያ መንግስት የቀረበውን ሐሳብ መሰረት በማድረግ በትዕዛዝ ቁጥር 54/1961 የአዋሽ ብሔራዊ ፓርክ እና በትዕዛዝ ቁጥር 59/1962 የሰሜን ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ ተቋቋሙ፡፡

6. የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ድርጅት በደንብ ቁጥር 65/1963 መሰረት ህጋዊ ዕውቅና ተሰጠው፡፡ እስከ 1968 ድረስ የድርጅቱ አጠቃላይ ተግባራትና ግልጋሎቶች የሚከናወኑት ከተቋማትና ግለሰቦች ተውጣጥቶ በተዋቀረ ቦርድ ክትትል ነበር፡፡ የኢትዮጵያ የደንና የዱር እንስሳት ባለስልጣን ነሐሴ 30 ቀን 1972 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ በመስከረም 5/1980) በአዋጅ ቁጥር 192/1972 የተቋቋመ ሲሆን፣ ይተዳደር የነበረውም በቦርድ ነበር፡፡

7. አደጋ ላይ ያሉ እንስሳትና እፅዋት አለም ዓቀፍ ንግድ ስምምነት (CONVENTION ON INTERNATIONAL TRADE IN ENDANGERED SPECIES OF WILD FAUNA AND FLORA) በደንብ ቁጥር 14/1981 ተቀብላለች ፡፡ በጥር 21 ቀን 1985 ዓ.ም. በአዋጅ ቁጥር 41/1985 የኢትዮጵያ ደንና ዱር አራዊት ባለስልጣን ተግባርና ኃላፊነት ወደ ተፈጥሮ ሀብት ልማትና የአካባቢ ጥበቃ ሚኒስቴር እንዲተላለፍ ተወሰነ፡፡ ከዚህም በመቀጠል በአዋጅ ቁጥር 94/1986 ከደን ጋር የተያያዙ አንቀፆችን በማስቀረት የዱር እንስሳት ጥበቃ ባለስልጣን ራሱን ችሎ እንዲቀጥል ተደረገ፡፡ በአዋጅ ቁጥር 4/1995 የተፈጥሮ ሀብት ልማትና የአካባቢ ጥበቃ ሚኒስቴር ኃላፊነትና ተግባር ወደ ግብርና ሚኒስቴር እንዲዘዋወር ተደረገ፡፡

8. የዱር እንስሳት ጥበቃ ባለስልጣን ኃላፊነትና ተግባር በአዋጅ ቁጥር 120/1990 ለብዝሀ ህይወት ጥበቃና ምርምር ኢኒስቲትዩት ተሰጠ፡፡ ይህንን አዋጅ በአዋጅ ቁጥር 167/1991 በማሻሻል የዱር እንስሳት ጥበቃ ድርጅት እንደገና በባለስልጣን መስሪያ ቤትነት እንዲቀጥል ተደረገ፡፡ በ1996 ዓ.ም. ደግሞ የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 380/1996 በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ስር እንደ አንድ መምሪያ እንዲሆን ተወሰነ፡፡

9. በመጨረሻም ለዱር እንስሳት የተለየ ትኩረት እንዲያገኙ፣ ህብረተሰቡንና ሌሎችን ባለድርሻ አካላትን የሚያሳትፍ እና ቀጣይነት ያለው የዱር እንስሳት ሀብት ልማት እና ጥበቃ

በሀገራችን እንዲኖር ታስቦ የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/1999 ወጣ፡፡

10. የዚህ አዋጅ ዋና ዋና ዓላማዎችም፣

- የኢትዮጵያን የዱር እንስሳት ሀብት መጠበቅ፣ መንከባከብ፣ ማልማትና በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል፣
- የዱር እንስሳት ሀብትን አጠባበቅ፣ እንክብካቤና አጠቃቀም በሚመለከት መንግስት በዓለም ዓቀፍ ስምምነት የገባቸውን ግዴታዎች ለመፈፀም እንዲችል ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- በዱር እንስሳት ሀብት ላይ የተመሰረተ ቱሪዝም እንዲስፋፋና ኢንቨስትመንት እንዲበረታታ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣

የሚሉት ሲሆኑ፣

11. በአሁኑ ወቅት የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 575/2000 እንደገና የፌዴራል መስሪያ ቤት ሆኖ ተጠሪነቱ ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር እንዲሆን ተደርጎ ተቋቁሟል፡፡

12. ባለሥልጣኑ በሥሩ 10 ብሔራዊ ፓርኮችን (የሰሜን ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ፣ የባሌ ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ፣ የነጭ ሳር ብሔራዊ ፓርክ፣ የኦሞ ብሔራዊ ፓርክ፣ የኣብጃታ ሻላ ሐይቆች ብሔራዊ ፓርክ፣ አዋሽ ብሔራዊ ፓርክ፣ ጋምቤላ ብሔራዊ ፓርክ፣ አላጥሽ ብሔራዊ ፓርክ፣ ቃፍታ ሽራሮ ብሔራዊ ፓርክ፣ ገራይሌ ብሔራዊ ፓርክ) እና 2 መጠለያዎችን (ሰንቀሌ የቆርኬዎች መጠለያና ባቢሌ የዝሆኖች መጠለያ) ያስተዳድራል፡፡ በተጨማሪም አንድ የክልል መስተዳደር ፓርክን (ያንጉዲራሳ ብሔራዊ ፓርክን) በአደራ እያስተዳደረ ይገኛል፡፡

<u>የባለስልጣኑ ዓላማ፣ ሥልጣንና ተግባር ;</u>

***ዓላማ***

13. የባለስልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 575/2000 መሰረት የሚከተለው ዓላማ እንዲኖረው ተደርጓል፡-

- የአገሪቱ የዱር እንስሳት ሀብት እንዲለማ፣ እንዲጠበቅና ዘላቂነት ባለው መልኩ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ ፡፡

*ሥልጣንና ተግባር*

14. ባለስልጣኑ በማቋቋሚያ አዋጁ መሰረት የተለያዩ ሥልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል፡፡ ከነዚህም ውስጥ፡-

- የዱር እንስሳት ሀብት ልማትን፣ ጥበቃንና አጠቃቀምን በተመለከተ የፖሊሲና የህግ ረቂቅ እያዘጋጀ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀዱም በተግባር ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣
- በስሩ የተቋቋሙትን የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ያለማል፣ ያስተዳድራል፣ ህገ-ወጥ ተግባራት እንዳይፈፀሙባቸው ይከላከላል፣
- በውጭ ቱሪስቶች ለሚከናወን አደን ፈቃድ ይሰጣል፣
- ሆቴል፣ ካምፕ፣ ሎጅና ሌሎች አገልግሎቶች በዱር እንሰሳት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥ እንዲቋቋሙ ፈቃድ ይሰጣል፣
- ማንኛውም የዱር እንስሳት ወይም የዱር እንስሳት ውጤቶችን ከአገር ለማስወጣት ወይም ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት የሚያስችል ፈቃድና የጤና ምስክር ወረቀት ይሰጣል፣
- እንስሳት ውጤት በተሰጠው ፈቃድ ውስጥ ለተመለከተው ዓላማ መዋሉን ይቆጣጠራል፣ ውጤቱንም ይለካል፣
- የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች በዓለም የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ህብረት እንዲመዘገቡ ለማስቻል ዓለማቀፋዊ መስፈርት ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፣ እነዚህኑ መሰፈርቶች ጠብቀው መተዳደራቸውን ይከታተላል፣
- ለዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ የቴክኒክ ዕርዳታና ሌላም ድጋፍ ሊሰጡ ከሚችሉ ወገኖች ጋር ዓለም አቀፍ ግንኙነት ይመሰርታል፣
- የዱር እንስሳት ሀብትን አስመልክቶ ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸው ዓለም-አቀፍ ስምምነቶች ተግባራዊ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፣ለሚመለከታቸው ዓለም-አቀፍ ተቋማትም በየጊዜው ሪፖርት እያዘጋጀ ያስተላልፋል፡፡
- የዱር እንስሳትን በተመለከተ በማንኛውም ዓለም አቀፍ ስብሰባ ወይም ጉባኤ መንግስትን ይወክላል፣
- የዱር እንስሳት ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀምን በሚመለከት ጥናትና የስልጠና ፕሮግራም ያካሂዳል፣ ወቅታዊ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያቀነባብራል፣ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፣
- ለክልሎች በዱር እንሰሳት ልማትና ጥበቃ ረገድ አሰፈላጊውን እገዛ ይሰጣል፣ አሰፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ስልጣንና ተግባሩን ለሌሎች የፌደራልና የክልል መንግስት አካላት በውክልና ይሰጣል፣
- በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችም ሆነ ከጥበቃ ቦታዎች ውጪ በሚገኙ የዱር እንስሳት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ በሽታዎችን ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል፣

- ከፌደራል መንግስት ጋር በተገባ የኮንሴሽን ውል መሰረት በግል ባለሀብቶች የሚተዳደሩትን የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ይቆጣጠራል፣
- በመንግስት በጸደቀ ተመን መሰረት ለሚሰጠው አገልግሎት ዋጋ ያስከፍላል፣

የሚሉት ይገኙበታል፡፡

<u>የባለስልጣኑ አደረጃጀትና የሰው ሀይል</u>

15. የባለስልጣኑ ጽ/ቤት የሚመራው በተቋሙ የበላይ አመራር አካል በሆነው የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ሲሆን፣ የባለሥልጣኑ ተጠሪነት ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሆኖ በስሩ ለዋና ዳይሬክተሩ ተጠሪ የሆኑ 12 ዳይሬክቶሬቶች ይገኛሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ባለስልጣኑ 11 ብሔራዊ ፓርኮችና 2 መጠለያዎችን ያስተዳድራል፡፡

16. ባለስልጣኑ ራሱን ችሎ እንዲቋቋም ሲደረግ፣ ከግብርና ሚኒስቴር የተዛወሩ 105 ወንድ እና 10 ሴት ሰራተኞች የነበሩት ሲሆን፣ በ2001 ዓ.ም. 111 ወንድ እና 28 ሴት ሰራተኞች ተቀጥረዋል፡፡ በሰኔ 2003 ዓ.ም ባለስልጣኑ አዲስ የተረከባቸው የፓርኮች ሰራተኞችን ጨምሮ 653 ወንድ እና 101 ሴት እንዲሁም መደብ ያልተሰጣቸው 12 ጨምሮ በድምሩ 766 ሰራተኞች አሉት፡፡

<u>የባለስልጣኑ የፋይናንስ ምንጭ</u>

17. የባለስልጣን መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ ከመንግስት ከሚመደብ በጀት ሲሆን፣ በ2001 ዓ.ም. በጀት አመት ከተመደበው ብር 7,035,993.00 ስራ ላይ የዋለው ብር 5,924,512.77 ወይም 84% ሲሆን፣ በ2002 በጀት ዓመት ደግሞ ብር 19,145,650.44 ተመድቦ ከዚህ ውስጥ ስራ ላይ የዋለው ብር 18,211,710.13 ወይም 95% ነው፡፡ እንዲሁም መ/ቤቱ ለሚያካሂደው ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ብር 1,382,581.70 በ2002 ዓ.ም. ተገኝቷል፡፡

<u>የኦዲቱ አላማ</u>

18. ባለስልጣኑ ከተቋቋመበት አላማ አንፃር፣ የአገሪቱ የዱር እንስሳት ሀብት እንዲለማ፣ እንዲጠበቅና ዘላቂነት ባለው መልኩ ጥቅም ላይ እንዲውል የማድረጉ ተግባር ብቃት ያለውና ውጤታማ መሆኑን እንዲሁም በዱር እንስሳት ላይ የተመሰረተ የቱሪዝም ልማት እንቅስቃሴ ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲሆን፣ ውጤቱ የሚጠበቀውን ያህል ሆኖ ካልተገኘም የአሰራር ግድፈቶችን ለይቶ ለማውጣትና የማሻሻያ ሀሳብ ለማቅረብ ነው፡፡

## <u>የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች እና መመዘኛዎች (AUDIT ISSUES AND EVALUATIVE CRITERIA)</u>

19. ከላይ የተመረጠውን የኦዲት ዓላማ ለማሳካት ሦስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች የተመረጡ ሲሆን እነርሱም ፡-

    1. *የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ስርዓተ-አስተዳደር መኖሩን፣ ተግባራዊ መደረጉንና ውጤታማ መሆኑን መገምገም*
    2. *የዱር እንስሳት ሀብት ላይ የተመሰረተ ቱሪዝም ልማት እንቅስቃሴዎች መኖራቸውን፣ ተግባራዊ መደረጋቸውንና እና ውጤታማ መሆናቸውን መገምገም*
    3. *በአገሪቱ ያለውን የዱር እንስሳት ክምችት ለማወቅ፣ ለመጠበቅና የዘለቄታዊ አጠቃቀም ስልት ለመቀየስ የሚረዳ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ መኖሩን፣ ተግባራዊ መደረጉንና ውጤታማነቱን ማረጋገጥ*

*የሚሉት ናቸው፡፡*

20. እነዚህን ሦስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ኦዲት ለማድረግ 51 የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች ተዘጋጅተዋል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶች ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 1 ተያይዘዋል፡፡


## <u>የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ</u>

21. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (ETHIOPIAN PERFORMANCE AUDIT STANDARDS) እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ነው፡፡ የዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው ከ2000-2002 እና የ2003 በጀት አመት አጋማሽ ያሉትን የበጀት አመታት ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ነው፡፡ በባለስልጣኑ ስር ከሚተዳደሩ 13 የጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የአብጃታ-ሻላ ሐይቆች፣ የነጭ ሳር፣ የአዋሽ እና የባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርኮች፣ ከሰንቀሌ የቆርኬዎች መጠለያ እና ከባቢሌ የዝሆኖች መጠለያ የኦዲት ቡድኑ በአካል ተገኝቶ ጉብኝት በማድረግ፣ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች ቃለ መጠይቅ በማቅረብና መረጃዎችን በመገምገም መረጃ ሰብስቧል፡፡


22. በአካል ተገኝቶ መረጃ ባልተሰበሰበባቸው ሰባት የጥበቃ ቦታዎች ለስድስቱ መጠይቅ የተላከ ሲሆን ይህ ሪፖርት እስከተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ ከኦሞ ብሔራዊ ፓርክ፣ ከሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ፣ ከጋምቤላ ብሔራዊ ፓርክ ብቻ ለመጠይቆቹ ምላሽ የተገኘ ሲሆን ከሌሎቹ መልስ አልተላከም፡፡ በተጨማሪም ከደቡብ በበሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ እና ከኦሮሚያ የደን እና የዱር እንስሳት ኢንተርፕራይዝ ኃላፊዎችም መጠይቅ በማቅረብ መረጃ ተሰብስቧል፡፡

# የሥራ ሂደት መግለጫ (PROCESS DESCRIPTION)


## የዱር እንስሳት ጥበቃ ንዑስ የስራ ሂደት ሥዕላዊ መግለጫ




## የዱር እንስሳት ልማት ንዑስ የሥራ ሂደት ሥዕላዊ መግለጫ



## የዱር እንስሳት አጠቃቀም ንሁስ የሥራ ሂደት ሥዕላዊ መግለጫ



# ክፍል ሁለት

## ግኝቶች

### *የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ስርዓት አስተዳደር መኖሩን ተግባራዊ መደረጉንና ውጤታማነቱን በተመለከተ*

*<u>በሀገሪቱ የሚገኙ የዱር እንስሳት ዓይነት፣ብዛትና ሥርጭት ጥናት ስለመከናወኑ እና የጥበቃ ቦታዎች ህጋዊ ሰውነት ማግኘታቸውን በተመለከተ</u>*

23. በሀገሪቱ የሚገኙ የዱር እንስሳት ዓይነት፣ ብዛት፣ሥርጭት ሊጠና ይገባል፡፡ በጥናቱ መሰረት የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች (የዱር እንስሳት ጥብቅ ክልል፣ የዱር እንስሳት መጠለያና የቁጥጥር አደን ቀበሌዎች)እንደ ዱር እንስሳቱ ያሉበት ደረጃ የሚጠበቁባቸው ሥፍራዎች ሊከለሉ ይገባል፡፡ በጥናት የተለዩትና የተከለሉት የጥበቃ ቦታዎች ሕጋዊ ሰውነት ሊያገኙ ይገባል፡፡

24. ይሁን እንጂ በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙ የዱር እንስሳት ብዛትና ስርጭትን ለማወቅ እንዲቻል አጠቃላይ ቆጠራ በመሬትና በአየር ለማድረግ የሚያስችል የበጀትና የማቴርያል ድጋፍ የሚያስገኝ ሰነድ በ2000 በጀት አመት ለማዘጋጀትና ፈንድ ለማሰባበስብ በዕቅድ የተያዘ ቢሆንም በዕቅዱ መሰረት ሰነዱ አልተዘጋጀም፡፡ በአገሪቱ የሚገኙ የዱር እንስሳት አይነት፣ ብዛት እና ስርጭት ጥናቱም አልተከናወነም፡፡ይሁን እንጂ የጋምቤላ ብ/ፓርክ የዱር እንስሳት ሀብት ቆጠራ በ2002ዓ.ም. ተከናውኗል፡፡ በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ሥር የሚተዳደሩ 11 ብሔራዊ ፓርኮች እና 2 የዱር እንስሳት መጠለያ ጣቢያዎች በድምሩ 13 የጥበቃ ቦታዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ 13 የጥበቃ ቦታዎች ውስጥ ተከልለው ህጋዊ ሰውነት ያገኙት የአዋሽ ብ/ፓርክ (በአዋጅ ቁጥር 54/1961)፣ የሰሜን ተራሮች ብ/ፓርክ (በአዋጅ ቁጥር 59/1969) እና የአላጥሽ ብ/ፓርክ (በአማራ ብሔራዊ ክልል መስተዳደር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 38/1998) ብቻ ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ 10 የጥበቃ ቦታዎች ህጋዊ ሰውነት የላቸውም፡፡ ሕጋዊ ሰውነት ያገኘው የአዋሽ ብሔራዊ ፓርክ ይዞታው የአዋሽ ከተማ በፓርኩ ክልል ውስጥ እየተስፋፋና በሕገወጥ የቤት ግንባታና የመሬት ምሪት እየተካሄደ በዱር እንስሳቱና በመኖሪያ አካባቢያቸው ላይ ተጽዕኖ እየፈጠረ መሆኑን ፓርኩ እና የአዋሽ ፈንታሌ ወረዳ መስተዳደር ካደረጉት መጻጻፎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

25. ስለጉዳዩ የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ በአገሪቱ የሚገኙ የዱር እንስሳት ዝርያዎች አይነት፤ ስርጭትና የአኗኗር ሁኔታን በተመለከተ ከጥቂት ዓመታት በፊት የተዘጋጀ ጥናት መኖሩን እና ጥናቱም በመስሪያ ቤቱ ቤተ-መፃህፍት ውስጥ እንደሚገኝ፣ ነገር ግን ይህን መረጃ በየጊዜው ወቅታዊ የማድረግ ስራ በቀጣይ የሚሰራ መሆኑን፤ በተለይ በብሔራዊ ፓርኮች የዱር እስሳት አይነት፣ ብዛትና ስርጭትን ማጥናትን በተመለከተ፤ ስራው በርካታ ገንዘብ፤ የሰው ሃይልና ሎጂስቲክ የሚፈልግ በመሆኑ በሁሉም የጥበቃ ቦታዎች በአጭር ጊዜ ጥናቱን ማከናወን አስቸጋሪ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

26. ህጋዊ ሰውነት የሌላቸው የጥበቃ ቦታዎችን በተመለከተ ደግሞ በሰጡት ምላሽ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ዳግም ተካልሎ ህጋዊ የማድረግ ስራ በርካታ ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ የሚከናወን በመሆኑ በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚጠናቀቅ አይደለም፡፡ ነገር ግን ባለስልጣኑ እንደገና ከተቋቋመ ጀምሮ ለአራት የጥበቃ ቦታዎች (ለሁለት የዱር እንስሳት መጠለያዎች እና ለሁለት ብ/ፓርኮች) የዳግም ክለላ ጥናት ማድረጉን እንዲሁም ከአካባቢው ህብረተሰብ ጋር የዳር ድንበር ክለላውን በተመለከተ የምክክር አውደ ጥናት አካሂዷል፡፡ በቀጣይነት የጥበቃ ቦታዎቹን ህጋዊ ሰውነትና የይዞታቸውን ማረጋገጫ የሚደነግግ ህግ አርቅቆ ህጋዊ የማድረግ ስራ ብቻ የሚቀር መሆኑንና ገልጸዋል፡፡ በመጪዎቹ የአምስት አመት ስትራቴጅክ ዕቅድ /2003-2007/ ሁሉም የጥበቃ ቦታዎች በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የሚጠናቀቁ መሆኑን ገልዋል፡፡

27. የባለሥልጣኑ ኃላፊዎች ይህን ምላሽ ይስጡ እንጂ በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ቤተመፃህፍት ይገኛል የተባለው መረጃ በቤተ-መፃህፍቱ ሊገኝ አልቻለም፡፡ ባለስልጣኑ በተቋቋመባቸው ባለፉት ሦስት አመታት ውስጥ ጥናቱ ተሰርቶ ባይጠናቀቅም መረጃው የዱር እንስት ሀብትን በተመለከተ ለሚሰጡ የፖለሲ ውሳኔዎች እና የገንዘብም ሆነ ሌላ ሀብትን ለመመደብ መሰረት ከመሆኑ አንጻር እንዲሁም በባለሥልጣኑ ቀጣይ የአምስት አመት ስትራቴጅክ ዕቅድ /2003-2007/ ውስጥ ያልተካተተ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል አልተቻለም፡፡

28. ስለሆነም፣ በሀገሪቱ የሚገኙ የዱር እንስሳት ዓይነት፤ ብዛት፤ሥርጭት ጥናት ባለመከናወኑ ሀገሪቱ ምን ያህል የዱር እንስሳት ሀብትን እንዳላት በትክክል ማወቅ አልተቻለም፡፡ ይህም የዱር እንስሳት ሀብትን በተመለከተ በዘላቂነት ለመጠቀም ለሚሰጡ ውሳኔዎች መነሻ መረጃ (BASE LINE DATA) እንዳይኖር አድርጓል፡፡ የጥበቃ ቦታዎች ተካልለው ሕጋዊ

ሰውነት እንዲያገኙ አለመደረጉም ጥበቃ ቦታዎች ውስጥ ከፍተኛ መጠን ያለው ህገወጥ ተግባራት እንዲከናወን እና የጥበቃ ቦታዎቹ ስርዓተ ምህዳር እንዲናጋ ምክንያት ሆኗል፡፡

<u>ለዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች የፓርክ ማኔጅመንት ዕቅድ(PARK MANAGEMENT PLAN) መዘጋጀቱን በተመለከተ</u>

29. ለዱር እንስሳት ፓርኮችና መጠለያዎች የፓርክ ማኔጅመንት ዕቅድ (PARK MANAGEMENT PLAN) ተዘጋጅቶላቸው ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ የፓርክ ማኔጅመንት ዕቅዱ ሲዘጋጅም የአካባቢውን ህብረተሰብ ሊያሳትፍና ተጠቃሚነቱን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

30. በቀድሞው የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር በ1998-2002 ዓ.ም. በተዘጋጀው የአምስት አመት ስትራቴጂክ እቅድ መሰረት እንዲሁም መ/ቤቱ ለብቻው እንደ ባለሥልጣን ከተቋቋመ በኃላ ባለው ከ2000-2002ዓ.ም. ቀሪ የስራቴጂክ አመታት ውስጥ ለ10 የጥበቃ ቦታዎች የፓርክ ማኔጅመንት ዕቅድ ለማዘጋጀት በዕቅድ ተይዞ ነበር፡፡ በባለስልጣን መ/ቤቱ ከሚተዳደሩት 13 የጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የሰሜን ተራሮች ብ/ፓርክ በ2002 ዓ.ም.፣ የባሌ ተራሮች ብ/ፓርክ በ2000 ዓ.ም. እና የአዋሽ ብ/ፓርክ በ1984 ዓ.ም. እና በድጋሚ በ1996 ዓ.ም የፓርክ ማኔጅመንት ዕቅድ የተሰራላቸው ሲሆን፣ የባቢሌ የዝሆኖች መጠለያ ሙሉ ስራው ተጠናቆ መፅደቅ እንደሚቀረው በተጨማሪም አላጥሽ ብሔራዊ ፓርክ በረቂቅ ደረጃ እንደተጠናቀቀ ታውቋል፡፡ ለቀሩት የጥበቃ ቦታዎች የፓርክ ማኔጅመንት ዕቅዱ እንዳልተሰራላቸው ተረጋግጧል፡፡

31. የፓርክ ማኔጅመንት ዕቅድ ከተሰራላቸው የጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የአዋሽ ብ/ፓርክ እየተሰራበት የሚገኘው የፓርክ ማኔጅመንት ዕቅድ በ1996 ዓ.ም በተሠራው ሳይሆን በ1984 ዓ.ም. በተሰራው መሆኑን፣ የባሌ ብ/ፓርክ ደግሞ የፓርክ ማኔጅመንት እቅዱ ይሰሩበት የነበረ ቢሆንም አሁን ግን መተግበር እንዳቆሙ በስፍራው ጉብኝት ባደረግንበት ወቅት ከጥበቃ ቦታው ኃላፊዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

32. ጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣኑ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ ባለስልጣኑ እንደ አዲስ የተቋቋመና ሥራ የጀመረው ከሐምሌ 2000 ዓ.ም. ጀምሮ በመሆኑ በነዚህ ዓመታት ውስጥ የመ/ቤቱን የሰው ኃይል የማደራጀት፣ ፓርኮችን የመረከብና የዳር ድንበር ስራዎችን በመስራት ላይ ያተኮሩ በመሆኑ ለበርካታ ብ/ፓርኮች የፓርክ ማኔጅመንት ዕቅድ ለመስራት አለመቻሉን ገልጸዋል፡፡ በእነዚህ ጊዜያት በቅርቡ ለባቢሌ የዝሆኖች መጠለያ የፓርክ ማኔጅመንት ዕቅድ ዝግጅት እንደተጠናቀቀ ገልጸዋል፡፡

33. በቀጣዩም የእቅድ ዓመታት ለሌሎቹም እንደሚሰራላቸው ነገር ግን የፓርክ ማኔጅመንት ዕቅድ ከመሰራቱ በፊት የጥበቃ ቦታዎቹን ዳር ድንበር አካልሎ ማጠናቀቅ እንደ አንድ ቅድመ ሁኔታ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የስርአተ አስተዳደር ከተሰራላቸው የጥበቃ ቦታዎች የባሌ ተራሮች ብ/ፓርክ የፓርክ ማኔጅመንት ዕቅድ ከዱር እንስሳት ልማት፤ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ጋር ስለሚጋጭ ለጊዜው እንዲቆም መደረጉን ሲገልፁ፤ የአዋሽ ብ/ፓርክ ወቅታዊ የሆነውን የፓርክ ማኔጅመንት ዕቅድ ያለመጠቀም እንዲሁም የፓርክ ማኔጅመንት ዕቅዶች ሲዘጋጁ ህብረተሰቡን ባሳተፈ መልኩ ስለመሆኑ ምላሽ ለማግኘት አልተቻለም፡፡

34. ስለሆነም ለዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች የፓርክ ማኔጅመንት ዕቅድ (PARK MANAGEMENT PLAN) ተዘጋጅቶ ያለመተግበሩ በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የሚገኝ ስነምህዳርን የመለየትና በዘላቂነት የመጠበቅ ተግባር በረጅም ጊዜ እቅድ ላይ እንዳይመሰረት አድርጓል፡፡

<u>በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ ህገ-ወጥ ተግባራት</u>
<u>መከናወን/ አለመከናወናቸውን በተመለከተ</u>

35. በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የሚከናወኑ ህገ-ወጥ ተግባራት (ሰፈራ፤ የእርሻ ስራ፤ ግጦሽ ወዘተ..) ለመከላከል የሚያስችል የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ የሚከናወነውም የቁጥጥር ሥርዓት የአካባቢውን ሕብረተሰብ እና መስተዳድሮች ሊያሳትፍ ይገባል፡፡

36. በኦዲቱ ወቅት በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ስር በሚተዳደሩ የጥበቃ ቦታዎች ውስጥ ህገ-ወጥ ሰፈራ፤ የእርሻ ስራና ግጦሽ እንዲሁም ህገ-ወጥ የዱር እንስሳት አደን በኦሞ ብ/ፓርክ፤ በአብጃታ-ሻላ ሐይቆች ብ/ፓርክ፤ በሰንቀሌ የቆርኬዎች መጠለያ፤ በአዋሽ ብ/ፓርክ በባሌ ተራሮች ብ/ፓርክ፤ በጋምቤላ ብ/ፓርክ እና በባቢሌ የዝሆኖች መጠለያ የሚከናወን መሆኑ በመስክ ጉብኝት፣ ከጥበቃ ቦታ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ውይይት እና ከተሰበሰቡ መጠይቆች ታውቋል፡፡ (ዝርዝር ሁኔታው በሠንጠረዥ ተመልክቷል)

<u>ሠንጠረዥ 1</u>

| የጥበቃ ቦታው | ሕገ ወጥ ሰፈራ | ሕገ ወጥ እርሻ | ሕገ ወጥ ግጦሽ | ሕገወጥ አደን (ከ2000-2003 ዓ.ም.) | |
|---|---|---|---|---|---|
| ኦሞ ብ/ፓርክ | 500 ሰፋሪዎች | | 45 ሄክታር | ድፈርሳ<br>ዝሆን<br>አምባራይሌ<br>ጎሽ<br>ውድንቢ<br>ቀጭኔ | 3<br>1<br>4<br>14<br>2<br>1 |
| አብጃታ-ሻላ ብ/ፓርክ | 51828 ሰፋሪዎች<br>4 አንደኛ ደረጃ | 322 ሄክታር | 160 ሄክታር | ክርክሮ<br>ጅብ | 1<br>1 |

| የጥበቃ ቦታው | ሕገ ወጥ ሰፈራ | ሕገ ወጥ እርሻ | ሕገ ወጥ ግጦሽ | ሕገወጥ አደን (ከ2000-2003 ዓ.ም.) | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ት/ቤቶች | | | | |
| ሰንቀሌ የቆርኬዎች መጠለያ | 86 አባወራ ሰፋሪዎች | | ከ500 ሄክታር በላይ | ከርከሮ | 2 |
| አዋሽ ብ/ፓርክ | ቁጥራቸው በውል ያልታወቀ ጊዜያዊ ሰፋሪዎች (Seasonal Settlers) | | 48000 ሄክታር | አምባራይሌ<br>የሜዳ ፍየል<br>አጋዘን<br>ነብር<br>አንበሳ<br>ከርከሮ | 14<br>2<br>1<br>11<br>9<br>12 |
| ባሌ ተራሮች ብ/ፓርክ | 3 ቀበሌ | | | ነብር | 13 |
| በባቢሌ የዝሆኖች መጠለያ | በውል የማይታወቅ ወቅታዊ ሰፋሪዎች (Seasonal Settlers) | መጠኑ የማይታወቅ | መጠኑ የማይታወቅ | ዝሆን<br>የቆላ አጋዘን<br>አንበሳ<br>አምባራይሌ<br>ድኩላ | 9<br>1<br>2<br>9<br>1 |
| የጋምቤላ ብ/ፓርክ | | | | ነጭ ጆሮ ቆርኬ<br>ከርከሮ<br>ድኩላ<br>ፌቆ<br>ጎሽ<br>አንበሳ | 750<br>84<br>162<br>120<br>14<br>1 |
| ነጭ ሣር ብሔራዊ ፓርክ | ከ300 በላይ አባወራዎች (በአማካይ 100 ከብት በአንድ አባወራ) | መጠኑ ያልታወቀ | መጠኑ ያልታወቀ | | |
| ድምር | | ከ322 ሄክታር (መጠኑ ያልታወቀውን ሳይጨምር) | 48705 ሄክታር (መጠኑ ያልታወቀውን ሳይጨምር) | | 1234 |

37. ከላይ እንደተመለከተው በጥበቃ ቦታዎቹ ውስጥ ህገወጥ የሆነ ሰፈራ በቋሚነት እና በጊዜያዊነት፣ ህገወጥ እርሻና ግጦሽ፣ እንዲሁም ህገወጥ አደን እየተከናወነ እንደሚገኝ ታውቋል፡፡



በአብያታ-ሻላ ብ/ፓርክ ውስጥ ከብቶች እና በባቢሌ የዝሆኖች መጠለያ ውስጥ ግመሎች ለግጦሽ ተሰማርተው በከፊል



በአብያታ ሻላ ብሔራዊ ፓርክ ውስጥ ከተሰሩት አራት ትምህርት ቤቶች አንዱ

38. ይህን ጉዳይ በተመለከተ የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ የሰፈራ፣ የእርሻና የግጦሽን በተመለከተ በመጠይቁ የሰፈረው አሃዝ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥም ሆነ መቃወም እንደሚያስቸግር ነገር ግን ሁሉም የጥበቃ ቦታዎች ከላይ ከተጠቀሱት ጫናዎች ነፃ ያለመሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ ለእነዚህና ለሌሎች አሉታዊ ተፅዕኖዎች በዋናነት መነሻ የሆኑት የህዝብ ቁጥርና ተጓዳኝ ፍላጎቶች መጨመርና በዕቅድ ላይ የተመሰረተ የመሬት/ የተፈጥሮ ሀብት/ አጠቃቀም ስልት ያለመቀየስ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

39. በመቀጠልም በዚህ ዙርያ ባሉት ባለድርሻ አካላት መካከል የተቀናጀ አካሄድ አለመኖራቸው፣ እነዚህ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ለዱር እንስሳት ጥበቃ ስፍራነት በሚከለሉበት ወቅት የነበረው የሕዝብ ቁጥርና ሰው ሰራሽ ጫና በጣም ውስን እንደነበረና ከዚህም የተነሳ የዕምቅ ሀብቱና የዱር ብዝሀ-ህይወት ይዘቱ በጥሩ ሁኔታ እንደነበር ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ የሕዝብ ቁጥርና ሰው ሰራሽ ጫና በከፍተኛ ሁኔታ በመጨመሩ የሰፈራ፣ እርሻና ግጦሽ መስፋፋት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱን ገልጸዋል፡፡ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ የአቅም ውስንነት፣ የጥበቃ ቦታዎች ወቅታዊ ሁኔታን ያገናዘበ የፓርክ ማኔጅመንት ዕቅድ ያለመኖር፣ በየደረጃው ያሉት የባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማነስ፣ ከዚህም የተነሳ በጥበቃና ልማቱ ስራዎች ላይ የአካባቢውን ህብረተሰብ ተሳትፎ አናሳ መሆኑንና የባለቤትነት ስሜት ያለመዳበር እንዲሁም በባለድርሻ አካላት መካከል የተቀናጀ አሰራር /አካሄድ/ ያለመዳበር መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

40. የዱር እንስሳት ህገ-ወጥ አደንን በተመለከተ ደግሞ በመጀመሪያ ደረጃ በሁሉም ጥበቃ ቦታዎች ያለው ህገ-ወጥ አደን በፐርሰንት ማስቀመጥ ለጊዜው ቢያስቸግርም ትርጉም ባለው መልኩ መቀነሱን ገልጸዋል፡፡ የህገወጥ አደኑን መንስኤ እንደ ጥበቃ ቦታውና የዱር እንስሳው ዓይነት ሁኔታ የሚለያይ መሆኑን፣ ለምሳሌ በባቢሌ ዝሆኖች መጠለያ ውስጥ ዝሆን የሚገደለው በአብዛኛው በሰውና በዝሆኑ መካከል ከሀብት ጋር (በተለይ በውሃ) የተነሳ ከሚከሰት ከግጭት ጋር በተያያዘ መሆኑን፣ በኦሞ ብ/ፓርክ ደግሞ በአብዛኛው ለጥርሱ ሲባል እንደሚገድሉት የሚታወቅ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ እንደ ነጭ ጆሮ ቆርኬ፣ አምባራይሌና ድፈርሳ የመሳሰሉት ስጋቸው ለምግብነት ስለሚውሉ ለዚሁ አላማ ሲባል እንደሚገደሉ ገልጸዋል፡፡ እንደ ከርከሮና የመሳሰሉት በአዋሽ፣ ሰንቀሌና አብጃታ-ሻላ ሊገደል የሚችለው ማለትም ሰብላቸውን ስለሚበላባቸው ሲሆን በጋምቤላና በኦሞ አካባቢ ግን ለምግብነት እንደሚገደሉ ገልፀዋል፡፡ እንደ አንበሳና ነብር የሚገደሉት ደግሞ ከብቱ

በሚበላበት አርብቶ አደር ሲሆን በአዋሽ ላይ ይህንን የተመለከተ በጥበቃ ቦታ ኃላፊዎች የተገለጸው ቁጥር ግን የጥበቃ ቦታው ሊሸከመው ከሚችለው የአንበሳ ቁጥር መጠን (CARRING CAPACITY OF THE PARK) በላይ የተጋነነ መሆኑን በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልፀዋል፡፡

41. ይሁን እንጂ በእኛ አስተያየት፣ በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የሚከናወኑ ህገ-ወጥ ተግባራት ለመከላከል የተዘረጋው የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት ደካማ በመሆኑና በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የሚከናወኑ ህገወጥ ተግባራት ለመግታት ባለመቻሉ በሀገሪቱ ለሚደረገው የዱር እንስሳት ሀብት ልማት ስራ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ከመፍጠሩም ባሻገር ሀገሪቱ ከዘርፉ መግኘት የሚገባትን ጥቅም ሊያሳጣ ይችላል፡፡

<u>በዱር አንስሳት የጥበቃ ቦታዎች ውስጥና አካባቢ
የልማት እንቅስቃሴዎች ከመከናወኑ በፊት አካባቢያዊ
ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት መካሄዱን በተመለከተ</u>

42. በማንኛውም የዱር እንስሳት ጥበቃና መዘዋወርያ ቦታዎች ውስጥም ሆነ አካባቢ የሚታቀድ የልማት እንቅስቃሴ ከመካሄዱ አስቀድሞ ከጥበቃ በቦታዎቹ ጠቅላላ የማኔጅመንት እቅድ (GENERAL MANAGEMENT PLAN)፣ የማኔጅመንት ዞን ዕቅድ (MANAGEMENT ZONE PLAN) ወይም የልማት ፅንሰ ሀሳብ እቅድ (DEVELOPMENT CONCEPT PLAN) አንፃር የተጠናና የባለሥልጣኑን/ የጥበቃ ቦታውን ይሁንታን በማግኘት የፀደቀ ዝርዝር የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ (ENVIRONMENT IMPACT ASSESSMENT) ሊኖር ይገባል፡፡

43. ይሁን እንጂ በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የልማት እንቅስቃሴ ከመካሄዱ አስቀድሞ የአካባቢ ተፅዕኖ ቅኝት (ENVIRONMENT IMPACT ASSESSMENT) ከጥበቃ ቦታዎቹ የማኔጅመንት ዞን ዕቅድ (MANAGEMENT ZONE PLAN) ወይም የልማት ፅንሰ ሀሳብ እቅድ (DEVELOPMENT CONCEPT PLAN) አንፃር ተገምግመው በዱር እንስሳቱና በአካባቢያቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አለመፍጠሩ ከተረጋገጠ በኋላ የፀደቁ ስለመሆኑ ማረጋገጫ በኦዲቱ ወቅት ተጠይቆ አልቀረበልም፡፡

44. በጥበቃ ቦታዎች አካባቢ በሦስተኛ ወገን የሚከናወኑ የልማት እንቅስቃሴዎች ልማቱ ከመፈቀዱ በፊት በጥበቃ ቦታው ላይ ወይም በዱር እንስሳቱ ላይ ሊያሳድር ስለሚችለው ተፅዕኖ ልማቱ በታቀደበት ቦታ የሚገኙ የጥበቃ ቦታ ፅ/ቤቶች እና የባለሥልጣን መ/ቤቱ አስተያየት በጥናቱ ውስጥ እንዲካተትበት ወይም እንዲያውቁት እንደማይደረግ በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ችለናል፡፡

45. በአሁኑ ወቅት የግንባታ ስራቸው የተጠናቀቁ እና በሂደት ላይ ያሉ በጥበቃ ቦታዎች አካባቢ ከሚካሄዱ የልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ፡- በአብጃታ ሻላ ብ/ፓርክ የሶዳ-አሽ ፋብሪካና የእንጉዳይና አልጌ ምርት፣ በባቢሌ የዝሆኖች መጠለያ የፍሎራ ኢኮ-ፓወር ፕሮጀክት በጥበቃ ቦታዎች ላይ ሊያስከትሉ ስለሚችሉት አሉታዊ ተፅዕኖን በተመለከተ ጥናት አለመከናወኑን ወይንም ለመከናወኑ ማረጋገጫ አልቀረበም፡፡

46. ስለጉዳይ የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ የጥበቃ ቦታዎችን አስተዳደር ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ከተረከበው ወዲህ ሁሉም የልማት እንቅስቃሴዎች ከመካሄዳቸው አስቀድሞ ተገቢው የአዋጭነትና የአከባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናቶች እንዲከናወኑባቸው የተደረገ መሆኑን በዚህ ረገድ በአዋሽ ብ/ፓርክ በቅርቡ ስራ የጀመረው ሎጅ ለአብነት ያህል መጥቀስ እንደሚቻል ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ቀደም ሲል ከርክክቡ በፊት ለእያንዳንዱ ጥበቃ ቦታዎች የተጀመሩት የልማት እንቅስቃሴዎች ከላይ የተጠቀሰውን አካሄድ ያልተከተሉበት ሁኔታ ስለነበር በአሁኑ ሰዓት በነዚህ ላይ የማስተካከል እርምጃ እየተወሰደ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

47. የሶዳአሽ ፋብሪካ የተቋቋመዉ የአብጃታ-ሻላ ሀይቆች ብ/ፓርክን ህልውና ግምት ውስጥ ባላስገባ መልኩ በደርግ ስርዓት ሲሆን፣ አሁን እየተከሰተ ላለው የአብጃታ ሀይቅ መጠን ለመቀነስ ዋናው ምክንያት እንደሆነ፣ በአሁኑ ሰዓት የማዕድንና ኢነርጂ ሚ/ር የፋብሪካው አካባቢያዊ ተጽዕኖ በጥልቀት እንዲጠና በጠየቀው መሰረት እየተጠና መሆኑና የጥናቱ ውጤት በሚያመላክተው መሰረት የእርምት እርምጃ ይወሰዳል የሚል እምነት እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡

48. የእንጉዳይ እና አልጌ ምርትን በተመለከተ መሬቱ ለባለሀብቱ የተሰጠው የአብጃታ-ሻላ ብሔራዊ ፓርክ በኦሮሚያ ክልል ይተዳደር በነበረበት ጊዜና ባለሥልጣኑ ከመረከቡ በፊት መሆኑና ይህም ሁኔታ በፓርኩ አሰራር ላይ ችግር የፈጠረ በመሆኑ ከባለሀብቱና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመነጋገር ተገቢው የማስተካከል እርምጃ መወሰዱና በማስተካከያውም መሰረት በጭቱ እና ሻላ ሀይቆች መካከል የሚገኘውን መሬት ለኢኮ-ቱሪዝም እንዲያውሉት፣ ሌላ ከፓርኩ ወጣ ያለ ክፍል ደግሞ ለአልጌምርት እንዲሰጣቸው በተደረሰው ስምምነት መሰረት ለኢኮ-ቱሪዝም የተሰጣቸው ቦታን በሚመለከት ከባለስልጣን መ/ቤቱ ጋር ስምምነት መፈራረማቸውን ገልጸዋል፡፡

49. ባቢሌ ዝሆኖች መጠለያ ውስጥና አካባቢው ላይ ተጀምሮ የነበረው የፍሎራ ኢኮ-ፓወር ፕሮጀክት የመጠለያው ዳግም ክለላ ከመካሄዱ በፊት ሲሆን፣ ይህም በቀድሞው የግብርናና

የገጠር ልማት ሚኒስቴር የዱር እንስሳት ጥበቃ መምሪያ፣ የተፈጥሮ ጥበቃ ተቆርቋሪ አካላት ባደረጉት የተቀናጀ ርብርቦሽ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ከፍተኛ የመንግስት አመራር አካላት እንዲያውቁት ተደርጎ መፍትሄ እንዲያገኝ እንደተደረገና በመቀጠልም ህብረተሰቡን ጨምሮ ሁሉም ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ በኦሮሚያ ክልል ያለው የዳግም ክለላ ስኬታማ በሆነ መልኩ እንዲጠናቀቅ መደረጉን ገልጸዋል፡፡

50. ይሁን እንጂ የተጀመሩ የማስተካከያ እርምጃዎች ጥረት ቢኖርም፣ በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥና አካባቢ የሚከናወኑ የልማት እንቅስቃሴዎች ከመካሄዳቸው አስቀድሞ የአካባቢ ተፅዕኖ ቅኝት (ENVIRONMENT IMPACT ASSESSMENT) የጥበቃ ቦታዎቹ ላይ ከሚያደርስው አሉታዊ ተጽዕኖ አንፃር እንዲገመገሙ አለመደረጉና የጥበቃ ቦታው የየባለሥልጣኑ ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡበት አለመደረጉ የጥበቃ ቦታዎችን ስርዓተ ምህዳር (ECOSYSTEM) እንዲናጋ ምክንያት ሆኗል፡፡

<u>በሀገራችን ብቻ ለሚገኙና ለእልቂት ስጋት</u>
<u>ለተጋለጡ የዱር እንስሳት ጥበቃ እንዲደረግላቸው</u>
<u>የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ</u>

51. በሀገራችን ብቻ የሚገኙ የዱር እንስሳት (ENDEMIC) ዓይነት፤ ዝርያ ብዛት፣ ሥርጭትና የአኗኗር ሁኔታ ሊጠኑ ይገባል፡፡ በእልቂት ስጋት (ENDANGERD) ላይ ያሉ የዱር እንስሳት ዝርያዎች ጥበቃ እንዲደረግላቸው የሚያስችል ሥርዓትም ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

52. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በሀገራችን ብቻ የሚገኙ የዱር እንስሳት ዓይነት፤ ዝርያ ፤ብዛት፤ ሥርጭትና የአኗኗር ሁኔታ በተወሰኑት ላይ የተጠና ቢሆንም ሁሉንም ያካተተ እንዳልሆነ ተረጋግጧል፡፡ በእልቂት ስጋት ላይ ያሉ የዱር እንስሳት ዝርያዎች ጥበቃ እንዲደረግላቸው የሚያስችል ስርኣትም ለቀይ ቀበሮ "በኢትዮጵያ ቀይ ቀበሮ ጥበቃ ፕሮጀክት" ተቋቁሞ በባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ ውስጥ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን፤ የስዋይን ቆርኬዎች በመጠለያ ውስጥ እንዲጠበቁና እንክብካቤ እንዲያገኙ የሰንቀሌ የቆርኬዎች መጠለያ መቋቋሙን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ለተቀሩት ለእልቂት ስጋት የተጋለጡ ብርቅዬ የዱር እንስሳትን በተመለከተ መረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡

53. ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ሀላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በአለም አቀፍ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ህብረት (INTERNATIONAL UNION FOR CONSEVATION OF NATURE, IUCN) መስፈርት መሰረት በሀገራችን የሚገኙና በመጥፋት አደጋ ላይ

ከሚገኙ የዱር እንስሳት ዋልያ፣ ቀይ ቀበሮ፣ የዱር አህያና የግሬቭ የሜዳ አህያ የመሳሰሉት ብዛት ስርጭትና የአኗኗር ሁኔታ በተለያየ ጊዜያት ተጠንተዋል፡፡ በጥናቱም ዝርያቸው ለመጥፋት አደጋ እየተጋለጡ ስለሆነ ከዚህ ሁኔታም የሚወጡበት መንገድ በማመቻቸት ላይ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ለአብነት ያህልም የቀይ ቀበሮ ጥበቃ ፕሮግራም ቀበሮዎቹ ላይየሚደርሰውን የዕብድ ውሻ በሽታ ለመከላለል ጥረት በማድረግ ላይ መሆኑን፤ ዋልያንና የስዋይን ቆርኬ ቁጥርም በጥሩ ሁኔታ በማገገም ላይ መሆኑን፣ የዱር አህያ እና የግሬቭ የሜዳ አህያ ባለፉት አስር አመታት ስለ ሁኔታቸው በማጥናት የተሻለ ጥበቃ የሚያገኙበት ሁኔታ በመመቻቸት ላይ መሆኑን እና ገልፀዋል፡፡ ለጥፋት በመጋለጥ ላይ ላሉት እንደ አንበሳ፣ አቦሸማኔ፣ እና የዱር ውሻ ላሉት አጥቢ ሥጋ በል እንስሳት ለመከላከል የድርጊት መርሃ ግብር በቅርቡ የተዘጋጀ መሆኑን በመውጫ ስብሰባ ወቅት አብራርተዋል፡፡ ነገር ግን በአገሪቱ ውስጥ ከሚገኙት ብርቅዬ የዱር እንስሳት አይነት አንጻር ተጠና የተባለው በቂ ባለመሆኑ የተሰጠውን መልስ እንዳለ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

54. ይሁን እንጂ በሀገራችን ብቻ የሚገኙ የዱር እንስሳት ዓይነት፤ ዝርያ ብዛት፤ ሥርጭትና የአኗኗር ሁኔታ ለሁሉም ባለመጠናቱ ለእልቂት የተጋለጡት የዱር እንስሳት አይነትና ብዛት በመለየትና ለእልቂት እየተጋለጡ ያሉትን ትኩረት በመስጠት አስፈላጊውን እንክብካቤ ለማድረግ አያስችልም፡፡

<u>ከጥበቃ ቦታዎች ውጭ ያሉት የዱር እንስሳት</u>
<u>የሚጠበቁበትና የመኖሪያ አካባቢያቸው</u>
<u>የሚተዳደሩበት ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ</u>

55. ከዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች ውጭ ያሉት የዱር እንስሳትና የመኖሪያ አካባቢያቸው የሚተዳደሩበትና የሚጠበቁበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ይህም ሥርዓት ከተለያየ በሽታዎች የሚጠበቁበት እና ሕክምና የሚያገኙበትን ስርዓት ይጨምራል።

56. ይሁን እንጂ ከዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች ውጭ ያሉት የዱር እንስሳትና የመኖሪያ አካባቢያቸው የሚተዳደሩበት ደንብና መመሪያ እንደሌለ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል ፡፡

57. ስለጉዳዩ የኦሮሚያ ክልል የደንና የዱር እንስሳት ድርጅት ኃላፊዎች ተጠይቀው፣ በየደረጃው መዋቅር ስላለ በዛ በኩል ክትትል እንደሚደረግ ነገር ግን ከባለስልጣኑ ድጋፍ እንደማያገኙ ገልፀዋል፡፡ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት የቱሪዝም ቢሮ ኃላፊዎች ደግሞ ከጥበቃ ቦታዎች ውጭ ያሉትን የዱር እንስሳት በተመለከተ

የማስተዳደር ስልጣኑ በአዋጅ ለክልሉ ግብርና ቢሮ መሰጠቱንና በቅንጅት አብረው እንደሚሰሩ ገልፀዋል፡፡

58. የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ይህ የባለስልጣኑ ሥራ አለመሆኑን ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ በባለሥልጣን መ/ቤቱ መቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 575/2000 መሰረት፣ በዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ፖሊሲና ስትራቴጂ ላይ ከጥበቃ ቦታዎች ውጭ የሚገኙ የዱር እንስሳት የሀብት መጠንና ስርጭት ተጠንቶ በአግባቡ እንዲተዳደርና እንዲጠበቅ መደረግ እንዳለበት በመቀመጡ፣ እንዲሁም ከጥበቃ ቦታ ውጭ ያሉትን የዱር እንስሳትን ከበሽታዎች የመከላከል ሥራን እና ለክልሎች አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት በግልጽ የተቀመጠ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

59. ስለሆነም ከዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች ውጭ ያሉት የዱር እንስሳትና የመኖሪያ አካባቢያቸው የሚተዳደሩበትና የሚጠበቁበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ባለመደረጉ ከጥበቃ ቦታዎች ውጭ የሚገኙ የዱር እንስሳት የሀብት መጠንና ስርጭት እንዲሁም የጤንነታቸው ሁኔታ እንዳይታወቅና ተገቢው ጥበቃና ክትትል እንዳይደረግላቸው አድርጓል፡፡

<u>በዱር እንስሳት ላይ የሚደርሱትን የተፈጥሮና የሰው ሰራሽ አደጋዎችን አስቀድሞ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ</u>

60. በዱር እንስሳት ላይ የሚደርሱትን የተፈጥሮና የሰው ሰራሽ አደጋዎችን አስቀድሞ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት የሚመለከታቸውን አካላት ባሳተፈ መልኩ ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

61. በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የተቋቋመ የዱር እንስሳት በሽታ መከላከል ሥርዓት አልተዘረጋም፡፡ ነገር ግን በግብርና ሚኒስቴር ሀገራዊ የእንስሳት በሽታ መከላከል ሥርዓትን ለዚሁ ተግባር እንደሚጠቀሙ ተገልፆልናል፡፡ በዋና መስሪያ ቤቱ ደረጃ እና በአዋሽ ብ/ፓርክ ከሚገኙት 2 የዱር እንስሳት የጤና ባለሙያ በስተቀር በተቀሩት የጥበቃ ቦታዎች የዱር እንስሳት ጤና ባለሙያ ያለመኖሩ ተረጋግጧል፡፡

62. በባሌ ተራሮች ብ/ፓርክ ከ2000-2003 ዓ.ም. 223 ቀይ ቀበሮ በራቢስ እና ካናይን ደስቴምበር በሚባሉ በሽታ መሞታቸውን፣ በአብጃታ-ሻላ ብ/ፓርክ ቁጥሩ በውል ያልታወቀ ትንሹ ቆልማሚት የአእዋፍ ዝርያ በአልጌ መመረዝ ምክንያት እንደሞቱ፣ በሰንቀሌ

የቆርኬዎች መጠለያ 1 የስዋይን ቆርኬ በአንትራክስ በሽታ መሞቱን ከየጥበቃ ቦታዎቹ ኃላፊዎች ተገልፆልናል፡፡ በናሙና የመስክ ጉብኝት ባደረግንባቸው በአብጃታ ሻላ፣ በአዋሽ፣ በነጭ ሳር፣ በባሌ ተራሮች ብ/ፓርኮች እንዲሁም በሰንቀሌ የቆርኬዎች እና በባቢሌ የዝሆኖች መጠለያዎች የቤት እንስሳት ከዱር እንስሳቱ ጋር ተቀላቅለው በግጦሽ ላይ ተሰማርተው እንዲሁም በሰንቅሌ የቆርኬዎች መጠለያ ውስጥ በአካባቢው ህብረተሰብ በህገ-ወጥ መንገድ በእሳት የተቃጠለ ከፍተኛ መጠን ያለው መሬት ተመልክተናል፡፡

63. የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ የዱር እንስሳት በሽታ መከላከል ሥርዓት መዘርጋቱን፣ ይህም ከሀገራዊ የእንስሳት በሽታ መከላከል ሥርዓት ጋር የተጣጣመ መሆኑን፣ የዱር እንስሳት በሽታ መከላከል ስርኣት በዱር እንስሳት ልማት፤ ጥበቃና አጠቃቀም ኦፕሬሽናል ማኗዋል ውስጥ መመልከት እንደሚቻል ገልጸዋል፡፡ የተጠቀሰው ችግር የተፈጠረው የሥርዓት ያለመኖር ሳይሆን የዱር እንስሳት ጥበቃ ሥርዓትን ሙሉ ለሙሉ ያለመተግበር እና ህግን የማስከበር ችግር እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ ህግን ሙሉ ለሙሉ ለማስከበር እና ህብረተሰቡን የማሳመን ስራ በመስራት የቤት እንስሳት ወደ ዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች እንዳይገቡ የማድረግና የመቆጣጠር ስራ ጊዜ፤ የሰው ሃይልና ገንዘብ የሚፈልግ ስራ በመሆኑ ህብረተሰቡ ከተፈጥሮ ሀብት ላይ ካለው ጥገኝነት እስኪላቀቅ ድረስ የሚፈጠር ችግር እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ በመውጫ ስብሰባ ወቅት ደግሞ ወደፊት በባለሥልጣኑ የራሱ የሆነ የእንስሳት ሕክምና ተቋም ለማቋቋም መታቀዱን አስታውቀዋል፡፡

64. የቀይ ቀበሮን በተመለከተ፣ ከቀይ ቀበሮ ጥበቃ ፕሮግራም ጋር በመተባበር የበሽታውን ስርጭት ለመግታት ለቀበሮዎቹና በአከባቢው ለሚገኙ ውሾች ክትባት እየተሰጠ ከመሆኑ ባሻገር ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የበሽታ አሰሳ ጥናት እና እርምጃም በመወሰድ ላይ መሆኑን፣ ከጥበቃ ቦታው ኃላፊዎች እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ተብሎ የተሰጠው እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር የደረሰ ጉዳት እንጂ በቅርቡ የተከሰተ አለመሆኑን ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን የስንቀሌ ቆርኬዎች መጠለያ ውስጥ በህገወጥ መንገድ በእሳት የተቃጠለውን መሬት በተመለከተ መልስ ለመግኘት አልተቻለም፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ከክልል የግብርና ቢሮዎች ጋር የእነሱን ሥርዓት ለመጠቀም የተስማሙበት የመግባቢያ ሰነድ በኦዲቱ ወቅት ባለመቅረቡ እንዲሁም ተዘረጋ የተባለው ሥርዓት በየጥበቃ ቦታዎቹ ባለመዘርጋታቸው የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

65. በዱር እንስሳት ላይ የሚደርሱትን የተፈጥሮና የሰው ሰራሽ አደጋዎችን አስቀድሞ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተዘረጋው ሥርዓት ተግባር ላይ ባለመዋሉ ከቤት እንስሳት በሚነሳ በሽታ፣ በመኪና አደጋ እና በመሳሰሉት የዱር እንስሳቱ ለመሞታቸውና በአካባቢያቸው ላይ ጉዳት ለመከሰቱ ምክንያት ሆኗል፡፡

<u>የዱር እንስሳት በሰውና አካባቢያቸው ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ለማድረግ የቅድመ-መከላከል ሥርዓት መኖሩን በተመለከተ</u>

66. የዱር እንስሳቱም በሰው፤ በቤት እንስሳትና በሰብል ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ቅድመ-መከላከል ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ሥርዓቱም ጉዳት የሚያደርሱ የዱር እንስሳት ዓይነት፣ ምክንያታቸው እና ሊያደርሱት የሚችለው የጥፋት መጠን ሊጠና ይገባል፡፡

67. በኦዲቱ ወቅት በባቢሌ የዝሆኖች መጠለያ በዝሆኖችና በአካባቢው ህብረተሰብ መካከል በተለይም የውሃ እጥረት በመኖሩ አርብቶአደሮቹ ለእራሳቸውና ለከብቶቻቸው ያከማቹትን ውሃ ዝሆኖች እየመጡ ስለሚጠጡባቸውና ሰብላቸውንም ስለሚያበላሹባቸው ግጭት እንደሚፈጠር ታውቋል፡፡ በአዋሽ ብ/ፓርክ፤ በአብጃታ-ሻላ ሐይቆች ብ/ፓርክ እና በስንቅሌ የቆርኬዎች መጠለያ እንደ ከርከሮና የመሳሰሉት የአርሶ አደሩን ሰብል የሚበሉና የሚያበላሹ በመሆኑ እንዲሁም በሚበሉበት ወቅት በሚፈጠር ግጭት እንዲሁም እንደ አንበሳና ነብር የመሳሰሉት ደግሞ ከብቶቻቸውን ስለሚበሉባቸው ግጭት ከአካባቢው ነዋሪዎች ጋር እንደሚፈጠር ታውቋል፡፡ በዚህም ምክንያት እራሰቸውን፣ ከብቶቻቸውንና ሰብላቸውን ለመከላከል ሲሉ በአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚገደሉ ታውቋል፡፡

68. በባብሌ የዝሆኖች መጠለያ ችግሩን ለመከላከል የዝሆኖችን ወቅታዊ እንቅስቃሴ በመከታተል የአካባቢው ህብረተሰብ ዝሆኖቹ በሰው፣ በሰብልና በሌሎች ንብረቶች ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ጥንቃቄ እንዲያደርግ በተለያዩ የአካባቢው ቋንቋዎች በሐረሪ ሬድዮ ጣቢያ የቅድመ- መከላከል ጥንቃቄ መልዕክት እንዲተላለፍ እንደሚደረግ ከጥበቃ ቦታው ኃላፊ ተገልፆልናል፡፡

69. ይህንን በተመለከተ የባለስልጣን መ/ቤቱ ሃላፊዎች ተጠይቀው ሲመልሱ፣ የዱር እንስሳቱ መኖሪያ አካባቢ እየተጣበበና እየተረበሸ በመሄዱ የስርአተ ምህዳሩ (ECO-SYSTEM) መስተጋብር መናጋት ምክንያት የተከሰተ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በዚህም ወቅት የዱር እንስሳቱ በሰው ህይወትና ንብረት ላይ ጉዳት ያደርሳሉ፡፡ ስለሆነም ህብረተሰቡ የተፈጥሮ

አካባቢውን ሚዛን እንዲጠበቅና ስነ-ምህዳራዊ መስተጋብሩ እንዳይናጋ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ፣ የግጭት መከላከያ ማኑዋልና በራሪ ፁሁፎችን በማሰራጨት በመስራት ላይ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ከግንዛቤ ማስጨበጫ በተጓዳኝ ትልቁ መፍትሄ ተደርጎ የተወሰደው ቁሳዊ የተፈጥሮ ይዘታቸው ያልተለወጠ የዱር እንስሳት መኖሪያ አካባቢዎችን መፍጠርና የጥበቃ ቦታዎችን ስርዓት-አያያዝ ማጠናከር በመሆኑ ይህን ለማሳካት ባለሥልጣን መ/ቤቱ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

70. ይሁን እንጂ በተግባር የሚታይ፣ ውጤታማ ሥራ በአፋጣኝ ባለመሠራቱ፣ በዱር እንስሳትና በህብረተሰቡ መካከል ግጭት እየተፈጠረ በመሆኑ የዱር እንስሳቱ በሰውና በንብረት ላይ ውድመት እያደረሱና እነርሱም ደግሞ በህብረተሰቡ ለመገደላቸው ምክንያት ሆኗል፡፡

<u>በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ ሰው ሰራሽ እና ተፈጥሮአዊ ለውጦች ክትትል /ECOLOGICAL MONITORING/ መኖሩን በተመለከተ</u>

71. በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ ሰው ሰራሽ እና ተፈጥሮአዊ ለውጦች ክትትል /ECOLOGICAL MONITORING/ ሊደረግ ይገባል፡፡ የክትትሉ ውጤት ሊተነተንና ተገምግሞ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

72. በኦዲቱ ወቅት የኦዲት ቡድኑ በናሙና ከተመለከታቸው የጥበቃ ቦታዎች ውስጥ በነጭ ሳር ብ/ፓርክ ውስጥ የሚገኘው ሳር የዱር እንስሳቱን የሚያጠቁ ተባዮች በማፍራቱና ለዱር እንስሳቱ ምቹ ባለመሆኑ ይህን ለመከላከል በሚል ሰፊ የሆነ መሬት በእሳት መቃጠሉን ተመልክተናል፡፡



በነጭ ሳር ብሔራዊ ፓርክ በዕሳት የተቃጠለው መሬት

73. በአብጃታ-ሻላ ሀይቆች ብ/ፓርክ ባለፉት አምስት አመታት አካባቢው ለሰጎኖቹ ለመታቀፍ አመቺ ባለመሆኑ ሊፈለፈሉ ያልቻሉ ከ600 በላይ የሚሆኑ የሰጎን እንቁላሎች በጥበቃ ቦታው መጋዘን ውስጥ ተከማችተው ይገኛሉ፡፡ በጥበቃ ቦታው ከዚህ ቀደም ቁጥራቸው ከሰባ በላይ የሚሆኑ ሰጎኖች የነበሩ ቢሆንም በቅርቡ ሰባት የታቀፉ እንቁላሎችን ሳይጨምር 18 ሰጎኖች ብቻ መኖራቸው የተገለፀልንና በስፍራው በመገኘት ለመመልከት ተችሏል፡፡

74. በተጨማሪም የአብጃታ ሀይቅን መሰረት አድርጎ በ1976 ዓ.ም. የተቋቋመው የሶዳ አሽ ፋብሪካ ሲቋቋም ከተተከለው የውሃ መሳቢያ ፓምፕ ውሃው ከ3 ኪ.ሜ. በላይ በመቀነሱና ከፓምፑ በመራቁ፣ ፋብሪካውም ውሃውን ለመሳብ የሚጠቀሙባቸው የውሃ መሳቢያ ፓምፑና ማስተላለፊያ ቱካዎች ውሃውን በመከተል ወደ ውስጥ እየተስፋፉ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡



**የሶዳ አሽ ፋብሪካ ከአብያታ ሐይቅ ለመሳብ የተዘረጋ የውሃ መሳቢያ**

75. በአጠቃላይ ሲታይ፣ በጥበቃ ቦታዎች ውስጥና አካባቢ ሰው ሰራሽ እና ተፈጥሮአዊ ለውጦች ክትትል /ECOLOGICAL MONITORING/ ባለመደረጉ በዱር እንስሳቱና የመኖርያ አካባቢያቸው ላይ ለሚደርሱ አሉታዊ ክስተቶች ለመከላከልና በወቅቱ ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ አላስቻለም፡፡

## *የዱር እንስሳት ሀብት ላይ የተመሰረተ ቱሪዝም ልማት እንቅስቃሴዎች መኖራቸው፣ ተግባራዊ መደረጋቸውንና ውጤታማ መሆናቸውን መገምገምን በተመለከተ*

<u>በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የተዘረጉ የመሰረተ-ልማት አውታሮችን በተመለከተ</u>

76. ጎብኚዎች የቱሪስት መስህቦች የሆኑትን የጥበቃ ቦታዎችን በሙሉ ተዘዋውረው ለመጎብኘት የሚያስችሉ በተጨማሪ ለዱር እንስሳቱ ጥበቃ ለማድረግ እና የጥበቃ ቦታዎቹን ከህገወጥ አድራጊዎች ለመከላከል በቂ የሆነ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች፣ የቱሪስት ማረፊያ ስፍራዎች፣ ለቱሪስት አገልግሎት መስጫ ተቋማት ሊገነቡ ይገባል፡፡

77. ይሁን እንጂ በጥበቃ ቦታዎቹ ውስጥ ለውስጥ የተሰሩ መንገዶች ከጥበቃ ቦታዎቹ ስፋት አንፃር በቂ ካለመሆናቸውም በላይ ለተሽከርካሪ አስቸጋሪና የማይመቹ ከመሆናቸውም ባለፈ ጥገና ለማድረግ የሚሞከረው በሰው ሀይል ብቻ እንደሆነ ታውቋል፡፡ የቱሪስት አገልግሎት መስጫ ተቋማትን በተመለከተ በ4 የጥበቃ ቦታዎች ብቻ ካሉት የሎጅ አገልግሎት ውጭ ለቀሪዎቹ ቦታዎች የሌለ መሆኑ ተገልጧል፡፡ (ዝርዝሩ በሰንጠረዥ 2–ተመልክቷል) በኦዲቱ የመስክ ጉብኝት ባደረገበት በአብጃታ-ሻላ ብ/ፓርክ ክልል ውስጥ በሻላ ሀይቅ ዳርቻ ላይ የጥበቃ ቦታው በኦሮሚያ ክልል ይተዳደር በነበረበት ወቅት አንድ ባለሀብት ፈቃድ አግኝተው የሎጅ ግንባታ ጀምረው የነበረ ቢሆንም፣ ግንባታው መቋረጡ ተውቋል፡፡ በሰንቀሌ የቆርኪዎች መጠለያ ውስጥ አንድ የቱሪስት መረጃ ማዕከል በመገንባት ላይ መሆኑን ተመልክተናል፡፡

<u>ሠንጠረዥ 2</u>

| የመ/ልማት አይነት | አዋሽ | ያንጉዲራሳ | ባቢሌ | ሰንቀሌ | አብያታ ሻላ | ባሌ ተራሮች | ገራይሌ | ነጭ ሳር | ኦሞ | ጋምቤላ | ሰሜን ተራሮች | አላጥሽ | ቃፍታ ሽራሮ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የጥበቃ ቦታ ስፋት(በኪ.ሜ. ስኬር) | 756 | 4731 | 6982 | 54 | 887 | 2200 | 3858 | 514 | 3566 | 5061 | 412 | 2666 | 5000 |
| በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የመንገድ ርዝመት በኪ.ሜ. | 250 | 70 | 420 | 140 | 263 | 70 | 520 | 120 | 197 | 320 | 300 | 260 | 115 |
| የማረፊያ ስፍራ ቁጥር /ካምፕ ሳይት/ | 7 | 3 | 3 | 6 | 5 | 14 | 1 | 3 | 4 | 6 | 13 | 10 | 1 |
| የሎጅ ቁጥር | 2 | - | - | - | - | 1 | - | - | 1 | - | 1 | - | - |

78. ስለጉዳዩ የባለሥልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ የጥበቃ ቦታዎች የመሰረተ ልማት በተመለከተ በአጭር ጊዜ የሚከናወን ሳይሆን ረጅም እቅድ ተይዞ ደረጃ በደረጃ የሚሟላ መሆኑን፤ የሎጅ ስራን በተመለከተ በፖሊሲ የግል ባለሀብት ሚና መሆኑንና በዚሁ መሰረት በነጭ ሳር፤ በሰሜን ተራሮች፤ በባሌ ተራሮች፤ በአብጃታ-ሻላ ሐይቆች እና በአዋሽ ብሔራዊ ፓርኮች ጥያቄው ቀርቦ እየተስተናገደ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በአብጃታ-ሻላ ብሔራዊ ፓርክ ተጀምሮ የተቋረጠውን የሎጅ ግንባታ በተመለከተ ፓርኩ በኦሮሚያ ክልል ይተዳደር በነበረበት ወቅት ተሰጥቶ የተቋረጠ የነበረና ከርክክቡ በኋላ ግን ግንባታው እንዲቀጥል ከባለሀብቷ ጋር ስምምነት መደረሱን ገልፀዋል፡፡ የውስጥ ለውስጥ መንገድን በተመለከተ ስራው እየተካሄደ ያለው በሰው ኀይል መሆኑ የአካባቢውን ህብረተሰብ ለማበረታታት እንደሆነና ሌላው የመንገድ ስራ የመንገዶች ባለስልጣን ኃላፊነት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

79. በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የተገነቡት የመሰረተ-የልማት አውታሮች በቂ ባለመሆናቸው የጥበቃ ቦታዎችን ሙሉ ለሙሉ ተዘዋውሮ ማየት ካለማስቻሉ በተጨማሪ የቱሪስቶችን ቁጥር ለመጨመር በሚደረገው ጥረት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡

<u>በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ ለሚከናወኑ የቱሪዝም</u>
<u>አንቅስቃሴዎች አጋዥ የሆኑ ምልክቶች</u>
<u>መኖራቸውን በተመለከተ</u>

80. በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ ለሚከናወኑ የቱሪዝም እንቅስቃሴዎች አጋዥ የሆኑ መረጃ ሰጪ ምልክቶች፤ የጎብኚዎች ማስተናገጃ የመግቢያ በርና የትኬት መቁረጫ ቢሮዎች፤ የጥበቃ ክልል ወሰን ምልክቶች በሁሉም የጥበቃ ቦታዎች ሊኖሩ ይገባል፡፡

81. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ የመስክ ጉብኝት ባደረገባቸው በአብጃታ-ሻላ ሀይቆች ብ/ፓርክ በፓርኩ ሠራተኞች ከሚደረግ ገለፃና ከሚሰጠው የአቅጣጫ ምሪት ውጭ የትኛው መንገድ ወዴት እንደሚወስድ፣ በዚያ አካባቢ ምን አይነት መስህብ እንዳለ የሚያሳዩ አቅጣጫ ጠቋሚ ፤ ለቱሪስት ማረፊያነት የተፈቀዱ ቦታዎች እና በጥበቃ ቦታ ውስጥ የተከለከሉ ተግባራትን ማስገንዘቢያ እና አቅጣጫ ጠቋሚ ገላጭ ምልክቶች ያለመኖራቸው ተረጋግጧል፡፡

82. በሰንቀሌ የቆርኬዎች መጠለያ መጠለያው የሚገኝበት ሥፍራ ከዋናው መንገድ 10 ኪሎ ሜትር ወደ ውስጥ ስለሚገባ ወደ ጥበቃ ቦታው የሚወስደው መንገድ ላይ አቅጣጫ ጠቋሚ

ምልክቶች በተወሰነ እርቀት ላይ መተከላቸው፣ ነገር ግን በመጠለያው የመግቢያ በር፣ የትኬት መቁረጫ ቢሮ እና የጥበቃ ቦታው ክልል ስለመሆኑ የሚገልጹ የማስገንዘቢያ ምልክቶች የሉም፡፡ በባቢሌ የዝሆኖች መጠለያ እንዲሁም በጋምቤላ ብሔራዊ ፓርክ የጎብኚዎች ማስተናገጃ ሥፍራ የመግቢያ በር፣ የትኬት መቁረጫ ቢሮ፤ የጥበቃ ቦታው ክልል ስለመሆኑ ማስገንዘቢያ ምልክቶች ያለመኖራቸው በተጨማሪም ታውቋል፡፡

83. ስለሁኔታው የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በአብጃታ-ሻላ ሀይቆች ብ/ፓርክ ከተረከቡት ጀምሮ ዋናው ትኩረታቸው ስርዓት ምህዳሩን አደጋ ላይ የጣሉትን ህገ-ወጥ ድርጊቶች መቀልበስ እንደነበር ገልጸው፣ አሁን ደግሞ ማኔጅመንቱን በሰው ኀይልና በሎጀስቲክስ በማጠናከር ላይ በመሆኑ የፓርኩን የአቅጣጫ ጠቋሚ ምልክቶች ጨምሮ ሌሎች መሰረተ-ልማቶች በመስራትና በማደስ ላይ የሚገኙ መሆኑን፤ ሰንቀሌን በተመለከተ የቱሪስት እንቅስቃሴ የተጀመረው በቅርቡ ቢሆንም፣ በሩ አጠገብ ተነጣይ ሰፈር እየተሰራ ስለሆነ ይህን ቦታ እንደ ትኬት መቁረጫ በመጠቀም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣውን ጎብኚ ማስተናገድ እንደሚቻል ታሳቢ መደረጉን ገልፀዋል፡፡ የባቢሌ የዝሆኖች መጠለያን በተመለከተ ወደ መጠለያው የሚያስገባ መገንጠያ መንገድ ላይ ጠቋሚ ምልክት የነበረ ሲሆን በመንገድ ሥራ ምክንያት መነሳቱን ሲገልጹ ወደ መጠለያው በሚወስዱ መንታ መንገዶች ላይ እና በመጠለያ ጣቢያው ውስጥ ለምን ምልክት እንደሌለ እንዲሁም የጋምቤላ ብ/ፓርክ ምልክት አለመኖሩን በተመለከተ ምላሽ ለማግኘት አልተቻለም፡፡

84. በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የጎብኚዎች ማስተናገጃ የመግቢያ በርና የትኬት መቁረጫ ቢሮዎች፣ በጥበቃ ቦታ ውስጥና ወደ ጥበቃ ቦታ የሚወስዱ መንገዶችና መገንጠያዎች ላይ በቂ መረጃ ሰጪ ምልክቶች እና የጥበቃ ክልል ምልክቶች ባለመኖራቸው በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ ለሚደረገው ጉብኝት የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት ካለማስቻሉም በላይ ያለጥበቃ ቦታው ፍቃድ ለሚከናወኑ ህገወጥ ተግባራት ምክንያት ይሆናል፡፡

<u>የጥበቃ ቦታዎች በአካባቢው የሚገኘውን ሕብረተሰብ ተጠቃሚ የቱሪዝም መስህብ የያዘ የቱሪስት ፓኬጅ ስለመዘጋጀቱ</u>

85. የጥበቃ ቦታዎች የአካባቢውን ተፈጥሮአዊ፤ ባህላዊና ታሪካዊ የቱሪዝም መስህብ የያዘ የቱሪስት ፓኬጅ ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ የሚዘጋጀውም ፓኬጅ የቱሪስት ፍሰትን እና እንቅስቃሴን ሊገቱ የሚችሉ ባህላዊና አካባቢያዊ ተፅዕኖዎችን ማስወገድ በሚያስችል መልኩ ለሁሉም የጥበቃ ቦታዎች ሊዘጋጅና ተግባራዊ

ሊደረግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የአካባቢው ሕብረተሰብ ከጥበቃ ቦታው ተጠቃሚ የሚሆንበት አሠራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

86.በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት የጥበቃ ቦታዎች በነጭ ሳር ብ/ፓርክ የፓርኩ ፅ/ቤት ከዞኑ የማህበራት ማደራጃ ጋር በመተባበር ህገ-ወጥ ተግባራት ሲያከናውኑ የነበሩ ሰዎችን በተለያዩ የስራ መስክ እንደ ዓሳ አስጋሪዎች ማህበር፣ ለቱሪስት የጀልባ አከራዮች ማህበር፣ የቱሪስት አስጎብኚ ማህበር እና ህጋዊ የማገዶ እንጨት ለቃሚዎች ማህበር በማደራጀት በቁጥር ከ500 በላይ የሚሆኑ ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደረጉን፣ በአብያታ-ሻላ ኃይቆች ፓርክ በአብያታ ሐይቅ ዳርቻ ላይ በማህበር የተደራጁ የአካባቢው ሴቶች ለከብት ምግብነት የሚውል ጨው (የቦሌ አፈር) በመሰብሰብ እና በመሸጥ እንዲተዳደሩ መደረጉን፣ እንዲሁም ከውጭ ድርጅት በተገኘ እርዳታ ለአካባቢው ሕብረተሰብ አንድ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በፓርኩ ትይዩ መሠራቱን፣ በባሌ ተራሮች ብ/ፓርክ የአስጎብኚዎች ማህበር፣ የፈረስ አከራዮች ማህበር፣ የዕቃ ጫኝና አውራጆች ማህበር፣ የምግብ አብሳይ ማህበር፣ ባህላዊ እቃዎች አምራቾችና ሻጮች ማህበር እና የማገዶ ሻጮች ማህበር የተደረጁ መሆኑን፣ በአዋሽ ብ/ፓርክ በመግቢያ በሩ ላይ የእደ-ጥበብ አቅርቦት በማህበር በተደረጁ የአካባቢው ህብረተሰብ እየተሸጠ መሆኑን በውስጡ በሚገኘው ሎጅ ውስጥ የአካባቢው ህበረተሰብ ቅዳሜ እና እሁድ ለቱሪስቶች ባህላዊ ትርኢት የሚያሳዩ መሆኑን፣ በሰሜን ተራሮች ብ/ፓርክ በስድስት ማህበራት የአካባቢውን ህብረተሰብ በማደረጀት የቱሪስት አገልግሎት እንዲሰጡ እየተደረገ መሆኑ የተገለፀልን እና የተወሰኑትን በሥፍራው በመገኘት ለመመልከት ችለናል፡፡

87.ነገር ግን የአካባቢውን ህብረተሰብ ከጥበቃ ቦታዎቹ ተጠቃሚ ማድረግን በተመለከተ የቱሪስት ፓኬጅ ወጥነት ባለውና ለሁሉም የጥበቃ ቦታዎች የሚያሳትፍ መልክ አልተዘጋጀም፡፡




በባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ ከተደራጁት ማህበራት ሁለቱ

88. የቱሪስት ፓኬጁ ወጥነት ባለውና ለሁሉም የጥበቃ ቦታዎች ያልተሰራበት ምክንያት የባለስልጣኑ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የቱሪስት ፓኬጅ ሊዘጋጅ የሚገባው በቱሪዝም ባለሙያ መሆኑን መጀመሪያ እንዲሰራበት ከተዋቀረው ዳይሬክትሬት ኃላፊነቱ ወደ ሌላ ዳይሬክቶሬት በመዘዋወሩ ያልተዘጋጀ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

89. የጥበቃ ቦታዎች ተፈጥሮአዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ የቱሪዝም መስህብ የያዘ የቱሪስት ፓኬጅ ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈና ወጥነት ባለው መልኩ ባለመዘጋጀቱ የጥበቃ ቦታዎችን ማራኪ ገፅታ ለይቶ የማስተዋወቅ ስራ በመስራት የቱሪስት ፍሰትን እንዲጨመርና የአካባቢው ህብረተሰብም ሆነ ሀገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ጥቅም እንድታገኝ የማያስችል መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡

<u>በዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች ውስጥ
የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎችን ለማገዝ የሚወጡ
መመሪያዎችን በተመለከተ</u>

90. በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የሚከናወን ማናቸውም የቱሪዝም እንቅስቃሴ በዱር እንስሳትና የመኖርያ አካባቢያቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳያሳድር ለማድረግ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተዘጋጅተው ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡

91. የቱሪዝም እንቅስቃሴው በዱር እንስሳትና የመኖርያ አካባቢያቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳያሳድር ለማድረግ በብሔራዊ ፓርኮች ውስጥ ለሚገነቡ ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚያገለግል ቴክኒካል ማንዋል ተዘጋጅቷል፡፡ ይሁን እንጂ በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ በቱሪስቶች/ጎብኚዎች/ተመራማሪዎች የሚደረግ እንቅስቃሴን ለመምራት የሚያስችል የቱሪስት መመሪያ /የቱሪስት ጋይድ/ በማዕከል ደረጃ ተዘጋጅቶ ለሁሉም የጥበቃ ቦታዎችና ለጥበቃ ቦታው ተጠቃሚዎች እንዲደርስ ያልተደረገ መሆኑን ለመረዳት ችለናል፡፡

92.የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ኃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፤ ስለቱሪዝም ሲታሰብ እንቅስቃሴው በዱር እንስሳቱና መኖርያ አካባቢያቸው ላይ የሚኖረውን አሉታዊ ተፅዕኖ መቀነስ አንዱ የኢኮ-ቱሪዝም መርህ መሆኑን፣ ይሁን እንጂ በአገራችን ያለው የቱሪስት ፍሰት ግን ይህን ስጋት የሚፈጥር አለመሆኑና ጥበቃ ቦታዎቹ ውስጥ ባልተፈለገ ሁኔታ ጉብኝት እንዳይካሄድ ቱሪስቶችን በበራሪ ፅሁፎች እንደሚያሳውቋቸው፤ ቱሪስቶች ደግሞ በየጥበቃ ቦታው መግቢያ በር ላይ የተገለፁትን መመሪያዎች የሚያውቁ መሆኑንና አብዛኞቹ መመሪያዎች አለማቀፋዊ ይዘት ያላቸው በመሆኑ ቱሪስቶች በቀላሉ የሚረዷቸው መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

93.የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ኃላሪዎች ይህን ይበሉ እንጂ በሀገራችን ያለው የቱሪስት ፍሰት ስጋት የሚፈጥር አይደለም መባሉ የቱሪዝሙን ቀጣይ እድገት ያላገናዘበ በመሆኑ፤ የቱሪስቶቹ ስብጥር የውጭና የሀገር ውስጥ ቱሪስቶችን የሚያካትት ከመሆኑ አንፃር ሁሉም ቱሪስት መመሪያዎችን ያውቃል የሚለው ምላሽ ተገቢ ባለመሆኑና በሁሉም የጥበቃ ቦታዎች ላይ የቱሪስት መመሪያዎች ባለመኖራቸው የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

94. በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የሚከናወን ማንኛውም እንቅስቃሴ ወጥ በሆነና ስርዓት ባለው መልኩ አለመከናወኑ በዱር እንስሳቱና በመኖርያ አካባቢያቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ሊታወቅ ይገባል፡፡

<u>በፍጆታዊ መልኩ/ CONSUMPTIVE / የዱር እንስሳት ሀብት አጠቃቀምን በተመለከተ</u>

95. በፍጆታዊ መልኩ / CONSUMPTIVE / የዱር እንስሳትን ጥቅም ላይ ለማዋል የዱር እንስሳት ህጋዊ አደን የሚካሄድባቸው ቦታዎችና ለአደን የሚውሉ የዱር እንስሳት ዓይነትና ብዛት ተለይተው ሊታወቁ ይገባል፡፡ በቁጥጥር የአደን ቀበሌና ከጥበቃ ቦታዎች ውጪ ያሉትን የዱር እንስሳት ሥርጭት በማያዛባ መልኩ የአደን ኮታ ሊወጣና ለስፖርታዊ አደንና

ሌሎች ጥቅሞች ሊውል ይገባል፡፡ አደኑም በተመደበው ኮታ መሰረት ለመከናወኑ ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

96. ለህጋዊ አደን የተፈቀዱ የዱር እንስሳት አይነት በዱር እንስሳት አጠቃቀም ደንብ ቁጥር 163/2001 ላይ ተደንግገዋል፡፡ በዚህም መሰረት የተቋቋሙ 18 የቁጥጥር አደን ቀበሌዎች ተለይተዋል፡፡ እነዚህም የአደን ቀበሌዎች ለተለያዩ ግለሰቦች/ድርጅቶች የተሰጡ እና 1 የህብረተሰብ የቁጥጥር አደን ቀበሌ መኖራቸው ታውቋል፡፡ በየሁለት አመቱም በፌደራል የዱር እንስሳት ባለሙያዎችና በክልል የዱር እንስሳት ባለሙያዎች የቁጥጥር አደን ቀበሌዎች ውስጥ ብቻ የሚገኙትን የዱር እንስሳት ቆጠራ በማከናወን የአደን ኮታ እንደሚወጣና አደኑ እንደሚከናወን ለመረዳት ችለናል፡፡ይሁን እንጂ የአደን ኮታ አወጣጡ ከጠቅላላ የሀገሪቱ የዱር እንስሳት ሀብት አንፃር እንደማይገመገም ተረጋግጧል፡፡

97. ስለጉዳዩ የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ በየሁለት አመቱ የሚደረጉት የቁጥጥር አደን ቀበሌዎች የክትትልና ግምገማ ሪፖርቶችና የአመቱ ኮታ የሚወሰነው ሳይንሳዊ መንገዶችን ተከትሎ በቁጥጥር አደን ቀበሌዎች በሚደረጉ የዱር እንስሳት ቆጠራና ኮታ ትመና መሰረት መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ በአገሪቱ የሚገኙ የዱር እንስሳት አይነት፣ ብዛት፣ ስርጭት መረጃ በሌለበትና ትክክለኛው የዱር እንስሳቱ ቁጥርና ስብጥር በማይታወቅበት ሁኔታ፣ የአንድ ቁጥጥር ቀበሌን መሰረት አድርጎ የሚወጣ የዱር እንስሳት ቆጠራና ኮታ አወጣጥ ሀገራዊ የዱር እንስሳቱን ብዛትና ስብጥር ያላገናዘበ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

98. ከዱር እንሳሳት ከቦታ ቦታ ተዘዋዋሪነት አንፃር የቁጥጥር አደን ቀበሌዎችን የዱር እንስሳት ስብጥር ብቻ በማጥናት የአደን ኮታ እንዲወጣና እንዲከናወን ማድረጉ አገሪቱ ያላትን ጠቅላላና ወቅታዊ የዱር እንስሳት መረጃ ያላገናዘበ መሆኑ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

<u>የዱር እንስሳትና የውጤቶቻቸው ዝውውር</u>
<u>ለመቆጣጠር የተዘረጋውን ሥርዓት በተመለከተ</u>

99. የዱር እንስሳትና ውጤቶቻቸው ዝውውር አግባብ ባለው መንገድ እንዲካሄድ ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ የሚዘረጋውም ሥርዓት የሚመለከታቸውን የፌዴራልና የክልል ባለድርሻ አካላትን ሊያሳትፍ ይገባል፡፡ የዱር እንስሳት መቆያ ስፍራ ለሚያቋቁሙ አካላት ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት ቦታው ዓለም ዓቀፍ የእንስሳት ደህንነት መስፈርቶችን ያሟላ መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ በህገወጥ መንገድ ሲዘዋወሩ የተያዙት የዱር እንስሳት በህይወት የተያዙትን ወደ ጥበቃ ሥፍራዎች ወይም

ወደ እንስሳት ማቆያ ሥፍራ፣ ከህገወጦች የተወረሱትን የዱር እንስሳት ውጤቶቻቸውን ደግሞ በጥንቃቄ የሚያዙበትና የሚወገዱበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

100. በሀገሪቱ ከጥበቃ ቦታዎች ውጭ ከሚመለከታቸው አካላት ፈቃድ ሳይሰጣቸው በተለያየ ቦታዎችና በተለያዩ ተቋማት (ግለሰቦች፣ ሆቴሎችና የንግድ ድርጅቶች፣ እና መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች) የዱር እንስሳት በህይወት ተይዘው እንደሚገኙ ታውቋል፡፡ የዱር እንስሳት የመያዝና የማዘዋወር ፍቃድ ለተሰጣቸውም የዱር አንስሳት ማቆያ ስፍራዎች አገሪቱ የገባቻቸውን አለም አቀፍ የዱር እንስሳት ደህንነት መስፈርቶችን ያሟላ ስለመሆኑ እንደማይረጋገጥ ታውቋል፡፡ በባቢሌ የዝሆኖች መጠለያ ጽ/ቤት ውስጥ ከህገወጦች እጅ የተያዙ ሶስት አምባራይሌዎች ጊዜያዊ መጠለያ በቆርቆሮና በሽቦ ተሰርቶላቸው እየተጠበቁ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ታይተዋል፡፡



በባሌ የዝሆኖች መጠለያ ጽ/ቤት ግቢ ውስጥ በጊዜያዊ መጠለያ የሚገኙ አምባራይሌዎች

101. ከ15 በላይ ክፍሎች ባሉት የባለስልጣኑ የዱር እንስሳት ውጤቶች እቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ከህገወጦች የተወረሱ ብዛታቸው 29,899 የሆነ 320 የዱር እንስሳት ውጤቶች አይነት በ12 ክፍሎች ውስጥ ተከማችተው እንደሚገኙ ታውቋል፡፡ ከዚህ ውስጥ 5287.5 ኪሎ ግራም የዝሆን ጥርስና ከዝሆን ጥርስ የተሰሩ ጌጣጌጦች ይገኙበታል፡፡ የዱር እንስሳት ውጤቶች ያሉበት ግምጃ ቤት ከወጣት ወንዶች ክርስትያን ማህበር ጋር አንድ ቅጥር ገቢ ውስጥ ያለ በመሆኑ ለጥበቃ አስቸጋሪ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ የዱር እንስሳት ውጤቶችን

በአግባቡ ለማስወገድ የሚያስችል አለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው መመሪያ ባለሥልጣኑ ቢኖረውም መመሪያውን መሰረት በማድረግ ውጤቶቹ እንዲወገዱ አልተደረገም፡፡ በዚህ ምክንያት በመጋዘኑ ውስጥ የተከማቹት ውጤቶች በተለይም የዱር እንስሳት ቆዳዎችና በታክሲደርሚ መልክ (ህይወት ያላቸው አስመስሎ በቅርጻቸው መልክ የተሰሩትን) በወቅቱና በአግባቡ እንዲወገዱ ባለመደረጉ ለረጅም ጊዜ በመጋዘን ተከማችተው ለብልሽትና ለጉድለት በመጋለጥ ላይ መሆናቸው ታውቋል፡፡



ከህገወጦች ተወርሰው በባለሥልጣኑ ግምጃ ቤት የሚገኙ የዝሆን ጥርሶች፣ከዝሆን የተሰሩ ጌጣጌጦች እና በነብር ቆዳ የተሰሩ ጌጦች በከፊል

102. ስለጉዳዩ የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ አንድ የዱር እንስሳት መቆያና መንከባከቢያ ማዕከል በባለስልጣኑ እና በቦርን ፍሪ ፋውንዴሽን ኢትዮጵያ በተባለ የበጎ አድራጎት ድርጅት ትብብር ሆለታ ላይ መቋቋሙን ገልጸዋል፡፡ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ አለም አቀፍዊ ድርጅት በመሆኑ አለምአቀፍ ስታንደርድ በጠበቀ መልኩ የማቆያ ቦታውን በመገንባት ላይ መሆኑ እና በከፊልም ተጠናቆ እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸውን እና በሕገወጥ መልክ ሲዘዋወሩ የተያዙት የዱር እንስሳት መንከባከብ ጀምሯል፡፡ በተጨማሪም በተለያዩ የመንግስት ተቋማት ይዞታ የሚገኙትን የዱር እንስሳት ወደዚህ ማቆያ ለማዘዋወር መታቀዱን ገልጸዋል፡፡

103. ከህገወጦች ተወርሰው በባለሥልጣኑ መጋዘን የተከማቹትን የዱር እንስሳት ውጤቶች በተመለከተ ባለስልጣኑ ከተቋቋመ ገና ሁለት አመት የሆነው በመሆኑ የወረሳቸውን የዱር እንስሳት ውጤቶች በዚህ በአጭር ጊዜ ውስጥ አጥርቶ መንቀሳቀስ አስቸጋሪ ቢሆንም ይህን ስራ ለማከናወን ሁኔታዎችን በማመቻቸት ላይ መሆኑናቸውን ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ በባለስልጣኑና በበጎ አድራጎት ድርጅቱ ትብብር ከተቋቋመው የዱር እንስሳት ማቆያ በተጨማሪ በግለሰቦች፣ በንግድ ተቋማት እና መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ በሌሎች ተቋማት ይዞታ ሥር የተለያዩ የዱር እንስሳት የሚገኙ በመሆኑና የእነዚህን የዱር እንስሳት አያያዝ፣ አጠባበቅና ጤንነታቸውን በተመለከተ ክትትል የሚደረግበት ሥርዓት ባለመኖሩ የተሰጠውን ምላሽ እንዳለ ለመቀበል ያስቸግራል። ከህገወጦች ተወርሰው የተያዙትን የዱር እንስሳት ውጤቶቻቸውን በአግባቡ ለማስወገድ የሚያስችል አለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው መመሪያ መኖሩና በሚያዝያ 2002 ዓ.ም. በባለሥልጣኑ የውስጥ ኦዲት ንብረቶቹ በአፋጣኝ እንዲወገዱ የቀረበ ሀሳብ ቢኖርም ተግባር ላይ እንዲውል ባለመደረጉ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

104. ስለሆነም አሠራሩ በወቅቱ ተግባራዊ አለመደረጉ፣ የዱር እንስሳትና ውጤቶቻቸው ዝውውር አግባብ ባለው መንገድ እንዲካሄድ ለመቆጣጠር የተዘረጋው ስርዓት በሀገሪቱ ውስጥ የሚከነወነውን ህገወጥ የዱር እንስሳትና ውጤቶቻቸውን ዝውውር ማስቆም ካለማስቻሉ በተጨማሪ ሀገሪቱ የገባቻቸውን አለምአቀፍ ስምምነት ትግበራ ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይቻላል፡፡

**በአገሪቱ ያለውን የዱር እንስሳት ክምችት ለማወቅ፣ለመጠበቅና የዘለቄታዊ አጠቃቀም ስልት ለመቀየስ የሚረዳ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ መኖሩን፣ተግባራዊ መደረጉንና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡**

<u>በባለድርሻ አካላት መካከል የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ለመፍጠር የሚያስችል ስርዓት ስለመዘርጋቱ</u>

105. በባለሥልጣን መ/ቤቱ፣ በፌዴራልም ሆነ በክልል ስለዱር እንስሳት የሚመለከታቸው አካላት በተናጠል ከዱር እንስሳት ጋር የተያያዙና በሥራቸው የሚገኙ መረጃዎችን አጠናቅረው ሊይዙ ይገባል፡፡ የተጠናቀሩትም መረጃዎች በየደረጃው ለሚመለከታቸው አካላት የሚተላለፍበት የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ለመፍጠር የሚያስችል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡ ባለሥልጣን መ/ቤቱም የአገሪቱን የዱር እንስሳት መረጃ አጠናቀሮ የሚይዝበት ዳታ ቤዝ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ በብሔራዊ ደረጃ የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የመረጃ ማዕከል ሊደራጅ ይገባል፡፡

106. ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሕገወጥ የዱር እንስሳት እና ውጤቶቻቸውን ዝውውር በተመለከተ ሥልጠና እንደሚሰጣቸው እና በሕገወጥ መንገድ የተያዙ የዱር እንስሳት ውጤቶቻቸውን ከአስፈላጊው መረጃ ጋር እንደሚለዋወጡ ታውቋል፡፡ ነገር ግን በሌሎች አካላት ከሚተዳደሩ የጥበቃ ቦታዎችና ከሌሎች ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል ባለድርሻ አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥ ለማድረግ የሚያስችል ስርዓት አለመኖሩ ታውቋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በብሔራዊ ደረጃ የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም መረጃ እንዳልተያዘ ተረጋግጧል፡፡

107. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣኑ መስሪያ ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በብሔራዊ ደረጃ የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም የመረጃ አውታር በማደራጀት በኩል ስራዎች እየተሰሩ መሆኑን፣ ነገር ግን ከፌዴራል እና ከክልል የሚመለከታቸው አካላት ጋር ያለው ግንኙነት ግን የተጠናከረ አለመሆኑን ገልፀዋል፡፡

108. በብሔራዊ ደረጃ አስፈላጊው የመረጃ ልውውጥ ቅንጅት ባለው መልክ እንዲካሄድ የሚያስችሉና ደረጃቸውን የጠበቁ የመረጃ መለዋወጫ ዘዴዎች ባለመኖራቸው የሀገሪቱን የዱር እንስሳት ሀብት የተመለከተ መረጃ ለማደራጀት አላስቻለም፡፡

**<u>በሀገሪቱ ስለሚገኙ የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች ዝርዝር መረጃና የተካሄዱ ጥናቶችን በተመለከተ</u>**

109. በሀገሪቱ ለሚገኙ የጥበቃ ቦታዎች ተፈጥሮአዊ፤ ባህላዊና ታሪካዊ ዝርዝር መረጃ ሊያዝ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የዱር እንስሳቱን እና አካባቢያቸውን በተመለከተ የተከናወኑ ጥናቶች በየጥናቱ አይነት እየተለየና እየተጠናቀረ በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ መረጃ ማዕከል ሊያዝ ይገባል፡፡ መረጃውም በየጊዜው ወቅታዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ መረጃውም በወቅቱና በአግባቡ ለተጠቃሚዎች የሚደርስበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

110. በሀገሪቱ ውስጥ በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ሥር 11 እና በክልል መንግስታት የሚተዳደሩ ደግሞ 9 በድምሩ 20 ፓርኮች 2 በባለሥልጣኑ እና አንድ በኦሮሚያ ክልል የሚተዳደሩ በድምሩ ሦስት የዱር እንስሳት መጠለያዎች በአጠቃላይ 23 የጥበቃ ቦታዎች እንዳሉ ታውቋል፡፡ በተጨማሪም 17 የቁጥጥር አደን ቀበሌዎች፣ ከአስር በላይ ክፍት የሆኑ የማደኛ ቦታዎች፣ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች እና የማህበረሰብ ጥበቃ ቦታዎች እንዳሉ ታውቋል፡፡ ይሁን እንጂ የሁሉንም የጥበቃ ቦታዎች ተፈጥሮዊ፤ ባህላዊ እና ታሪካዊ ዝርዝር መረጃ እንዲሁም በጥበቃ ቦታዎቹ ውስጥ ስለሚገኙ የዱር እንስሳትና አካባቢያቸው የተከናወኑ የተለያዩ ጥናቶች በተጠቃሚዎች አይነትና ፍላጎት መሰረት ተደራጅተው በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የመረጃ ማዕከል አለመያዛቸው ተረጋግጧል፡፡

111. ስለጉዳዩ የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ የተለያዩ መረጃዎችን በፅሁፍና በሶፍት ኮፒ በማደራጀት ፎቶግራፎችንም ሆነ ፅሁፎችን ለተገልጋይ እንዲደርስ በመረጃ ባለሙያው በኩል እንደሚሰራ ገልፀዋል፡፡ ሆኖም ግን በሚፈለገው ደረጃ እንዳልተሰራ ጠቅሰው ለዚህም ምክንያቱ የአቅም ችግር፤ የሰው ሀይል እጥረት፤ መረጃውን ሊሰጡ የሚገባቸው አካላት/ግለሰቦች በቅንነትና በተጠየቁት አግባብ በፍጥነት ለመስጠት ባለመቻላቸው የተከሰተ ችግር መሆኑን ገልጸዋል፡፡

112. በአገርአቀፍ ደረጃ የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም መረጃ ተደራጅቶ አለመያዙ የሀገሪቱን ነባራዊ የዱር እንስሳት ሀብት በተመለከተ መረጃ በወቅቱና በአግባቡ ለማግኘት አላስቻለም፡፡

**የጥበቃ ቦታዎችን ማራኪ ገፅታና የዱር እንስሳትና ውጤቶቻቸውን የማስተዋወቅ ስራን በተመለከተ**

113. የጥበቃ ቦታዎችን ማራኪ ገፅታ እና ለሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኙ የዱር እንስሳትና ውጤቶቻቸውን በተለያየ የመገናኛ ብዙሐንና በመረጃ መረብ የማስተዋወቅ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡

114. የሀገሪቱ የዱር እንስሳት ሀብትና የጥበቃ ቦታዎችን ማራኪ ገፅታ በቴሌቪዥን፣ በሬድዮ (በኢትዮጵያ ሬድዮና በተለያየ ኤፍ. ኤም ጣቢያዎች)፣ በሶኒክ እስክሪን፣ በቢልቦርዶች በትምህርት ሚኒስቴር የፕላዝማ ፕሮግራም፣ በአውቶብስ ማቆሚያዎች ወዘተ… የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ እንደሚሰራና በተጨማሪም በበራሪ ፁሁፎች /ብሮሸሮች /፣ መፅሄቶችና ፖስተሮች እንዲሁም በባለስልጣን መ/ቤቱ ድህረ ገፅ የማስታወቅ ስራ እንደሚከናወን ታውቋል፡፡ ነገር ግን በድህረ ገፁ ላይ የተቀመጡት፣ ያንጉዲራሳ፣ አብያታ ሻላ እና ኦሞ ብሔራዊ ፓርኮችን በተመለከተ የተቀመጡት መረጃዎች የጥበቃ ቦታዎቹን አሉታዊ ገጽታ ያካተቱ ሲሆን የገራይሌ ብሔራዊ ፓርክን በተመለከተ ምንም አይነት መረጃ አልተካተተም፡፡

115. ስለጉዳዩ የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ ያለው አንድ ባለሙያ በመሆኑና የሚፈለገው መረጃ ከሚመለከታቸው አካላት በወቅቱና በሚፈለገው ደረጃ ማግኘት ባለመቻሉ የተወሰነ ክፍተት ይታይ የነበረ በመሆኑ ችግሩን ለመፍታት ሁለት የዳሬክቶሬቱ ባለሙያዎች ያሉትን ብሔራዊ ፓርኮችና መጠለያዎች እንዲሁም የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተከፋፍለው መረጃዎቹን ወቅታዊ በማድረግ በኩል እንዲሰራ መደረጉን፣ የመረጃ ቅብብሎሽ ችግሩን ለመፍታት ሁሉም ዳይሬክቶሬትና ባለሙያ ከየራሱ የስራ ድርሻ አኳያ ሊሰጥ የሚገባውን መረጃ እንዲሰጥ በማኔጅመንት በተወሰነው መሰረት የተሻለ ሁኔታ እየታየ መሆኑና በቀጣይም አንድ አዲስ ሲኒየር የመረጃ ባለሙያ መቀጠሩን ገልፀዋል ፡፡

116. በመረጃ መረብ ላይ የጥበቃ ቦታዎችን አሉታዊ ገጽታ ማስቀመጥ ለጉብኝት የሚመጡ ቱሪስቶች ፍሰት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

**ስለዱር እንስሳትና የጥበቃ ቦታዎች**
**የሚደረገውን የግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ**
**በተመለከተ**

117. በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥና በአካባቢው ለሚገኘው ሕብረተሰብ ስለ ጥበቃ ቦታው ሁለንተናዊ ጠቀሜታ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ሊሰራ ይገባል፡፡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎቹም ያስገኙት ፋይዳ ሊገመገም ይገባል፡፡

118. በጥበቃ ቦታዎች አካባቢ ለሚገኙ ህብረተሰብ በሁለት መንገድ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ የሚሰራ ሲሆን ይህም በዋናው መስሪያ ቤት የመረጃ ትምህርት ህዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም ሲሰጥ፣ ሌላው ደግሞ የጥበቃ ቦታዎቹ በራሳቸው እቅድ የሚሰጡት የግንዛቤ ማስጨበጫ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ከ2000 ዓ.ም. እስከ 2003 ዓ.ም. ከ363,727 በላይ ለሚሆኑ ሰዎች ትምህርት መሰጠቱን ከየጥበቃ ቦታው ከቀረበው ሪፖርት ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቱ ያስገኘው ፋይዳ እንደማይገመገም ተረጋግጧል፡፡

119. ይህን ጉዳይ በተመለከተ የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው፣ ትምህርቱ በማህበረሰቡ ላይ ያመጣውን ለውጥ የመገምገሚያ መንገድ ስለሌለ አዎንታዊ ተፅዕኖው ለመገመት እንደሚያስቸግር ገልፀዋል፡፡

120. በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥና በአካባቢው ለሚገኘው ሕብረተሰብ ስለ ጥበቃ ቦታው ሁለንተናዊ ጠቀሜታ የተሰጡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ባለመገምገማቸው ያስገኙትን ውጤት ለማወቅና በቀጣይ አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ አያስችልም፡፡

**በጥበቃ ቦታዎች መካከል የሚደረግ**
**የልምድ ልውውጥ በተመለከተ**

121. ሀገር በቀል የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ዕውቀትና ልምዶችን በመለየት በማሻሻልና ተስማሚነታቸው በማረጋገጥ በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሊደረግ ይገባል፡፡ በጥበቃ ቦታዎቹ መካከልም የልምድ ልውውጥ ለማድረግ የሚያስችል ግንኙነቶች ሊፈጠሩ ይገባል፡፡

122. በኦዲቱ በስንቅሌ ቆርኬዎች መጠለያ የመስክ ጉብኝት ወቅት ከዚህ በፊት በአካባቢው ህብረተሰብ በሚፈፀም ህገ ወጥ የቆረኬዎች አደን ምክንያት ቁጥራቸው በከፍተኛ ሁኔታ ቀንሶ የነበረ የስዋይን ቆርኬዎችን ለመታደግ የአካባቢው ህብረተሰብ በጥበቃ ስራው ላይ አሳታፊ በማድረግና የአካባቢውን ህብረተሰብ ባህላዊ አስተዳደር ስርዓት( የገዳ ስርዓት)

በመጠቀም አንድ ቆርኬ እንደ አንድ የማህበረሰቡ አካል እንዲቆጠርና አንድ ቆርኬ የገደለ ሰው 100 ከብት ካሳ ወይም ጉማ እንዲከፍል በመታወጁ ህገ ወጥ አደኑ እንዲቆም በመደረጉ የቆርኬዎቹ ቁጥር እየጨመረ ለመምጣቱ አንዱ ምክንያት መሆኑን በጥበቃ ቦታው ኃላፊ ተገልፆልናል፡፡

123. በነጭ ሳር ብሄራዊ ፓርክ የጥበቃ ቦታው ከክልልና ከዞን መስተዳድር እንዲሁም ከከተማው ባለሀብቶች ጋር መልካም ግንኙነት ያለው በመሆኑ ከከተማው መስተዳድር ለጥበቃ ቦታው አጋዥ ሀይል እንዲሆኑ ሁለት የፖሊስ አባላት ተመድበው አገልግሎት በመስጠት ላይ መሆናቸው የተገለፅልንና እኛም በስፈራው በመገኘት መመልከት ችለናል፡፡ ይሁን እንጂ ሀገር በቀል የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ አጠቃቀም ዕውቀቶችና ልምዶችን በመለየትና በማሻሻል በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውሉና በጥበቃ ቦታዎቹ መካከል መልካም ተሞክሮ የልምድ ልውውጥ ለማድረግ የሚያስችል ስልት እንዳልተዘረጋ ተረጋግጦአል፡፡

124. ስለጉዳዩ የባለሥልጣኑ ኃላፊዎቹ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በአዋሽ ብሔራዊ ፓርክ ውስጥም በአርብቶአደሩ አካባቢ የህብረተሰቡን ልምድ በመለየት የተለምዶ የዘንባባ አጠቃቀም የአርብቶአደሩን የቅራኔ አፈታትና የሕዝብ ማስተዳደር ዘዴ እንደ ጅምር እየተጠቀሙበት መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን ከአንዱ የጥበቃ ቦታ ያለውን ጥሩ ተሞክሮ ወደ ሌሎች የጥበቃ ቦታዎች እንዲተላለፍ ያልተደረገበትን ምክንያት ምላሽ አልሰጡም፡፡

# ክፍል ሦስት

## መደምደሚያዎች

125. የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ስርዓት አስተዳደር መኖሩን ተግባራዊ መደረጉንና ውጤታማነቱን በተመለከተ፡

- በሀገሪቱ የሚገኙ የዱር እንስሳት ዓይነት፣ ብዛትና ሥርጭት ጥናት በብሄራዊ ደረጃ አለመከናወኑ፣
- አብዛኞቹ የጥበቃ ቦታዎች በወቅቱ ተካልለው ሕጋዊ ሰውነት እንዲያገኙ አለመደረጉ፣
- ለአብዛኞቹ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ስርዓተ- አስተዳደር ዕቅድ (PARK MANAGEMENT PLAN) ተዘጋጅቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣
- ከፍተኛ ወጪ እና ጊዜ ወጥቶባቸው የተሰሩ የጥበቃ ቦታ ስርዓተ- አስተዳደር ዕቅዶች ተግባራዊ አለመደረጋቸው፣
- በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ ህገ-ወጥ ሰፈራ፣ የእርሻ ስራና ግጦሽ እንዲሁም ህገ-ወጥ የዱር እንስሳት አደንን ለመከላከል የተዘረጋው ስርዓት ደካማ መሆኑ፣
- በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ እና አካባቢ የልማት እንቅስቃሴ ከመካሄዱ አስቀድሞ የአካባቢ ተፅዕኖ ቅኝት(ENVIRONMENT IMPACT ASSESSMENT) ከጥበቃ ቦታዎቹ የማኔጅመንት ዞን ዕቅድ (MANAGEMENT ZONE PLAN) ወይም የልማት ፅንሰ ሀሳብ እቅድ(DEVELOPMENT CONCEPT PLAN) አንፃር ተገምግመው በዱር እንስሳቱና በአካባቢያቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አለመፍጠሩ እንዲረጋገጥ አለመደረጉ፣
- በሁሉም በሀገራችን ብቻ ለሚገኙና ለእልቂት ስጋት ለተጋለጡ የዱር እንስሳትን በተመለከተ ጥናት አለመደረጉ፣
- ከጥበቃ ቦታዎች ውጭ ያሉት የዱር እንስሳትና የመኖሪያ አካባቢያቸው የሚተዳደሩበትና የሚጠበቁበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣
- በዱር እንስሳት ላይ የሚደርሱትን የተፈጥሮና የሰው ሰራሽ አደጋዎችን አስቀድሞ ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲቻል የተዘረጋው ስርዓት የተጠናከረና ውጤታማ አለመሆኑ፣

- ጉዳት የሚያደርሱ የዱር እንስሳት ዓይነትና የጥፋት መጠን የማጥናትና የዱር እንስሳቱም በሰው፣ በቤት እንስሳትና በሰብል ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ቅድመ-መከላከል ስራዎች በቂ አለመሆናቸው፤

- በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ ሰው ሰራሽ እና ተፈጥሮአዊ ለውጦች ክትትል/ECOLOGICAL MONITORING/ ተግባር አለመከናወኑ፤

126. የዱር እንስሳት ሀብት ላይ የተመሰረተ ቱሪዝም ልማት እንቅስቃሴዎች መኖራቸው፣ ተግባራዊ መደረጋቸውንና ውጤታማ መሆናቸውን መገምገምን በተመለከተ

- በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የተገነቡት የመሰረተ-ልማት አውታሮች በቂ አለመሆናቸው፣

- በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የጎብኚዎች ማስተናገጃ መግቢያ በርና የትኬት መቁረጫ ቢሮዎች፣ በቂ መረጃ ሰጪ ምልክቶች አለመኖራቸው፤

- የጥበቃ ቦታዎች ተፈጥሮአዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ የቱሪዝም መስህብ የያዘ የቱሪስት ፓኬጅ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፤

- በሁሉም የጥበቃ ቦታዎች ውስጥ ለሚደረጉ ማናቸውም እንቅስቃሴዎች በዱር እንስሳትና የመኖርያ አካባቢያቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳያሳድር ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተዘጋጅተው ተግባራዊ አለመደረጋቸው፤

- በፍጆታዊ መልኩ /ኮንሰፕቲቭ/ የዱር እንስሳትን ጥቅም ላይ ለማዋል የዱር እንስሳት ህጋዊ አደን የሚካሄድባቸው ቦታዎችና ለአደን የሚውሉ የዱር እንስሳት ዓይነት፣ ብዛትና ስርጭት ባልተጠናበትና በማይታወቅበት ሁኔታ መከናወኑ፤

- የዱር እንስሳትና ውጤቶቻቸው ዝውውር አግባብ ባለው መንገድ እንዲካሄድ ለመቆጣጠር የተዘረጋው ስርዓት በተጠናከረ መልኩ ከሚመለከተው አካላት ጋር በቅንጅት አለመተግበሩ፤

127. በአገሪቱ ያለውን የዱር እንስሳት ክምችት ለማወቅ፣ ለመጠበቅና የዘለቄታዊ አጠቃቀም ስልት ለመቀየስ የሚረዳ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ መኖሩን፣ ተግባራዊ መደረጉንና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥን በተመለከተ፣

- ሀገር አቀፍ የሆነ የዱር እንስሳትን የሚመለከት የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓት የሚመለከታቸውን አካላት ባሳተፈ መልኩ አለመዘጋጀቱ፤

- በሀገሪቱ ስለሚገኙ የጥበቃ ቦታዎች ዝርዝር መረጃ እንዲሁም የዱር እንስሳቱንና አካባቢያቸውን በተመለከተ የተከናወኑ ጥናቶች በተጠቃሚው አይነትና ፍላጎት ተደራጅተው በወቅቱና በአግባቡ ለተጠቃሚዎች እንዲድርስ አለመደረጉ፤
- ስለዱር እንስሳትና የጥበቃ ቦታዎች ጠቀሜታ ለህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ የሚሰራ ቢሆንም ያስገኙት ውጤት/ፋይዳ የማይታወቅና አስፈላጊው እርምጃ አለመወሰዱ፤
- በተለያዩ የጥበቃ ቦታዎችና አካባቢዎች ሀገር በቀል የዱር እንስሳት ልማት፤ ጥበቃና አጠቃቀም ዕውቀቶችና ልምዶች እንዲሁም መልካም ተሞክሮዎች ያሉ ቢሆንም በጥናት በመለየት የማሻሻልና በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውሉ የማይደረግ በመሆኑ፤

128. በአጠቃላይ በአገሪቱ የሚካሄደውን የዱር እንስሳትን ጥበቃና ልማትን አስመልክቶ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ እንቅስቃሴ እያደረገ ቢሆንም ሁሉም የጥበቃ ቦታዎች ህጋዊ ሰውነት ኖሮአቸውና  የማኔጅመንት ፕላን ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ አለመዋላቸው፣ በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የሚደረጉ ማናቸውም የቱሪዝም እንቅስቀሴዎች የሚመሩበት ወጥ የሆኑ መመሪያዎች ተዘጋጅተው ተግባራዊ አለመደረጋቸው እና በአገሪቱ ያለው የዱር እንስሳት ክምችትና የተያያዙ መረጃዎች አያያዝና የልውውጥ ሥርዓት አለመኖር፣ የዱር እንስሳትን ለመጠበቅና ለማልማት እየተደረገ ያለውን ጥረት ስኬታማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ስለሚያሳድር በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን የአሰራር ግድፈቶችና ድክመቶች፣ በአጠቃላይ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃን ሊያሻሽሉ ይችላሉ ተብለው የታመነባቸው የማሻሻያ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

129. የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ስርዓት አስተዳደር ስር የተገለፁ ግኝቶችን በተመለከተ፡-

- የዱር እንስሳት ሀብትን በተመለከተ በዘላቂነት ለመጠቀም ለሚሰጡ ውሳኔዎች መነሻ መረጃ (BASE LINE DATA) እንዲኖር አገር አቀፍ የዱር እንስሳት ቆጠራ የሚከናወንበትና የሀገሪቱ የዱር እንስሳት አይነት፣ ብዛትና ስርጭት መረጃ ማጠናቀር የሚቻልበት ሁኔታ መመቻቸት ይኖርበታል፡፡

- ለሁሉም የጥበቃ ቦታዎች ክለላ ጥናት የማድረግ፣ ከአካባቢው ህብረተሰብ እና የሚመለከታቸውን አካላት ጋር የዳር ድንበር ክለላውን በተመለከተ የምክክር አውደ ጥናት የማካሄድ እንዲሁም የጥበቃ ቦታዎቹን ህጋዊ ሰውነትና የይዞታቸውን ማረጋገጫ የሚደነግግ ህግ አርቅቆ ህጋዊ የማድረጉ ተግባር ትኩረት ተሰጥቶት ሊከናወንና ባፋጣኝ ሁሉም የጥበቃ ቦታዎች ህጋዊ ሰውነት እንዲያገኙ ሊደረግ ይገባል፡፡

- የጥበቃ ቦታዎችን በተቀናጀ መልኩ ለማስተዳደር ይቻል ዘንድ ወቅታዊ ሁኔታን ያገናዘበና የአካባቢውን ህብረተሰብ ተጠቃሚ ሊያደርግ የሚያስችል የፓርክ ማኔጅመንት ዕቅድ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል፡፡ ከዚህ ቀደም ከፍተኛ ወጪ እና ጊዜ ወጥቶባቸው የተሰሩ የፓርክ ማኔጅመንት ዕቅዶችንም በተገቢው መንገድ በማሻሻል የሚተገበሩበት ሁኔታ መመቻቸት ይኖርበታል፡፡

- በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የሚከናወኑ ህገ-ወጥ ተግባራት ለማስወገድ እንዲቻል ከፌደራል እስከ ክልል ቀበሌዎች የሚመለከታቸውን አካላት ያሳተፈና ወጥነት ያለው አደረጃጀት መፈጠር ይኖርበታል፡፡ በአሁኑ ወቅት በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የሚገኙት ሰፋሪዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ከጥበቃ ቦታዎች እንዲወጡ የሚደረግበት ሁኔታ ሊፈጠር ይገባል፡፡

- በዱር እንስሳት ጥበቃና መዘዋወርያ ቦታዎች ውስጥም ሆነ አካባቢ የሚታቀዱ የልማት እንቅስቃሴዎች በዱር እንስሳቱና የመኖሪያ አካባቢያቸው ላይ የሚያደርሱት አሉታዊ ተፅዕኖ በቅድሚያ በሚገመገምበት ወቅት በጥበቃ ቦታዎቹ ላይ ተፅዕኖ አለማድረሱ በጥበቃ ቦታው ወይም በባለስልጣኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

- ሀገሪቱ በገባችው አለም አቀፍ የሳይተስ ስምምነት መሰረት በሀገሪቱ/በግዛቷ/ ውስጥ በአስጊ ደረጃ ላይ ናቸው ተብለው የሚታመንባቸውን የዱር እንስሳት ዝርያዎች በመለየት ለሳይተስ ጽ/ቤት በማቅረብ እነዚህን ዝርያዎች በጋራ ለመንከባከብና ለመቆጣጠር የአባል ሀገራትን ትብብር ማግኘት እንዲቻል ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡
- ከጥበቃ ቦታዎች ውጭ የሚገኙትን የዱር እንስሳትን ከክልል መንግስታትና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት የሚተዳደሩበትና የሚጠበቁበት ሁኔታዎች መመቻቸት ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም የዱር እንስሳቱን ከበሽታዎች የመከላከል ሥራ እና ለክልሎች አስፈላጊው ድጋፍ በባለስልጣኑ ሊሰጥ ይገባል፡፡
- ጥበቃ ሥርዓትን ሙሉ በሙሉ በመተግበር እና ህብረተሰቡን የማሳመን ስራ በመስራት የቤት እንስሳት ወደ ዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች እንዳይገቡ የማድረግና የመቆጣጠር ስራ ተጠናክሮ መከናወን ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም በዕቅድ ላይ የተመሰረተ የበሽታ አሰሳ ጥናት በማከናወን ተገቢው እርምጃ በወቅቱ መወሰድ ይኖርበታል፡፡
- በሰውና በዱር እንስሳት መካከል የሚከሰት ግጭትን ለመከላከል ጉዳት የሚያደርሱ የዱር እንስሳት ዓይነት፣ ምክንያታቸው እና ሊያደርሱት የሚችለው የጥፋት መጠንን በማጥናትና የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ወቅቱን የጠበቀ የቅድመ-ጥንቃቄ መልዕክት ለህብረተሰቡ እንዲደርስ ሊደረግ ይገባል፡፡
- በጥበቃ ቦታዎች ውስጥና አካባቢ ሰው ሰራሽ እና ተፈጥሮአዊ ለውጦች ክትትል /ECOLOGICAL MONITORING/ ተግባር በየጊዜው በማከናወን አስፈላጊው እርምጃ በወቅቱ መወሰድ ይኖርበታል፡፡

130. የዱር እንስሳት ሀብት ላይ የተመሰረተ ቱሪዝም ልማት እንቅስቃሴዎች ስር የተገለፁ ግኝቶችን በተመለከተ፡-

    - ቱሪስቶች በየጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የሚያደርጉትን ጉብኝት የተመቻቸ እንዲሆንላቸው ለጎብኚዎች አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት እንዲሁም በክረምትና በበጋ ወቅቶች የሚያስኬዱና የጥበቃ ቦታዎቹን ሙሉ ለሙሉ ተዘዋውረው ለመጎብኘት የሚያስችሉ በቂ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች መገንባትና ተከታታይ የሆነ ጥገና ማከናወን ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም በሁሉም የጥበቃ ቦታዎች ውስጥ

የጎብኚዎች ማስተናገጃ የመግቢያ በርና የትኬት መቁረጫ ቢሮዎች፣ በጥበቃ ቦታ ውስጥና ወደ ጥበቃ ቦታ የሚወስዱ መንገዶችና መገንጠያዎች ላይ በቂ መረጃ ሰጪ ምልክቶች ሊኖሩ ይገባል፡፡

- የቱሪስት ፍሰትን እና እንቅስቃሴን ሊገቱ የሚችሉ ባህላዊና አካባቢያዊ ተፅዕኖዎችን ማስወገድ በሚያስችል መልኩ ለሁሉም የጥበቃ ቦታዎች የአካባቢውን ተፈጥሮአዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ የቱሪዝም መስህብ የያዘ የቱሪስት ፓኬጅ የሚመለከታቸውን አካላት ባሳተፈ መልኩ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡
- በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ በቱሪስቶች/ጎብኚዎች/ተመራማሪዎች የሚደረግ እንቅስቃሴን ለመምራት የሚያስችል የቱሪስት መመሪያ /የቱሪስት ጋይድ/ በማዕከል ደረጃ ተዘጋጅቶ ለሁሉም የጥበቃ ቦታዎችና ለጥበቃ ቦታው ተጠቃሚዎች እንዲደርስ መደረግ ይኖርበታል፡፡
- በፍጆታዊ መልኩ / CONSUMPTIVE / የዱር እንስሳትን ጥቅም ላይ ለማዋል የህጋዊ አደን ኮታ አወጣጥ ሂደት ከሀገራዊ የዱር እንስሳት ሀብት ክምችት መረጃ አንፃር መገምገም ይኖርበታል፡፡
- የዱር እንስሳት መቆያ ስፍራ ለሚያቋቁሙ አካላት ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት ቦታው ዓለም ዓቀፍ የእንስሳት ደህንነት መስፈርቶችን ያሚላ ስለመሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም በተለያዩ የመንግስት ተቋማት ይዞታ የሚገኙትን የዱር እንስሳት ወደ መኖርያ አካባቢያቸው ወይም ተገቢውን እንክብካቤ ወደሚያገኙበት ደረጃውን የጠበቀ የዱር እንስሳት ማቆያ ስፍራ መዛወር ያኖርባቸዋል፡፡
- በተለያዩ ጊዜያት ከህገወጥ አዘዋዋሪዎች ተወርሰው በባለስልጣኑ የእቃ ግምጃ ቤት ተከማችተው የሚገኙት የተለያዩ የዱር እንስሳት ውጤቶች በተገቢው መንገድ በአፋጣኝ መወገድ ይኖርባቸዋል፡፡

131. በአገሪቱ ያለውን የዱር እንስሳት ክምችት ለማወቅ፣ለመጠበቅና የዘለቄታዊ አጠቃቀም ስልት ለመቀየስ የሚረዳ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ስር የተገለፁ ግኝቶችን በተመለከተ፡-

- በባለሥልጣን መ/ቤቱ፣ በፌዴራልም ሆነ በክልል ስለዱር እንስሳት የሚመለከታቸው አካላት በተናጠል ከዱር እንስሳት ጋር የተያያዙና በሥራቸው የሚገኙ መረጃዎችን

አጠናቅረው መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡ ባለስልጣን መ/ቤቱም በየደረጃው በሚመለከታቸው አካላት የተጠናቀሩትን መረጃዎች የሚያሰባስብበትና የሚተላለፍበት የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓት ሊፈጥር ይገባል፡፡በተጨማሪም የአገሪቱን የዱር እንስሳት መረጃ አጠናቀሮ የሚይዝበት ዳታ ቤዝ ሊያደራጅ ይገባል፡፡

- የሁሉንም የጥበቃ ቦታዎች ተፈጥሮዊ፣ ባህላዊ እና ታሪካዊ ዝርዝር መረጃ እንዲሁም በጥበቃ ቦታዎቹ ውስጥ ስለሚገኙ የዱር እንስሳትና አካባቢያቸው የተከናወኑ የተለያዩ ጥናቶች በተጠቃሚዎች አይነትና ፍላጎት መሰረት ተደራጅተው በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የመረጃ ማዕከል ሊኖር ይገባል፡፡
- ስለ ዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች የማስተዋወቅ ስራ በሚሰራበት ወቅት የጥበቃ ቦታዎቹን አሉታዊ ገጽታ ያላካተተና ጎብኝዎችን በሚስብ መልኩ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡
- በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥና በአካባቢው ለሚገኘው ሕብረተሰብ ስለ ጥበቃ ቦታው ሁለንተናዊ ጠቀሜታ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ሊደረግና ያስገኘው ፋይዳም በየወቅቱ በመገምገም የማሻሻያ ስራዎች ሊሰሩ ይገባል፡፡
- ሀገር በቀል የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ዕውቀትና ልምዶችን በመለየት በማሻሻልና ተስማሚነታቸው በማረጋገጥ በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውሉ መደረግ ይኖርበታል፡፡

በአጠቃላይ በአገሪቱ የዱር እንስሳት ጥበቃና ልማትን በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ ለማደረግ የተጠናከረ የጥበቃ ቦታዎች አስተዳደር ሥርዓት፣ የቱሪዝም ልማትና የዱር እንስሳት ሀብትን የተመለከቱ መረጃዎች ተጠናቅረው መያዝ እና በአግባቡ ሥራ ላይ ለማዋል እና የተጠናከረ የክትትል እና የግምገማ ሥርዓት ለመዘርጋት የባለሥልጣን መ/ቤቱን፣ በዱር እንስሳት ሀብት ጥበቃና ልማት ዙሪያ የሚሰሩ የፌዴራል እና የክልል አስፈጻሚ አካላት እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ንቁ ተሳትፎ ይጠይቃል፡፡ ይህንንም ለማሳካት በፌዴራል እና በክልል የሚገኙ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግስት ተቆጣጣሪ አካላት ከፍተኛ ሚና እንደሚኖራቸው ይታመናል፡፡ በዚህ ሪፖርት የተገለጹት ግኝቶች፣ መደምደሚያዎች እና የማሻሻያ ሃሳቦች በቀጥታ ባለሥልጣን መ/ቤቱን የማይመለከቱ ቢኖሩ ባለሥልጣኑ በአዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት

ለመወጣት ስለሚያግዘው በተጠቀሱት ችግሮች ላይ የተሰጡትን የማሻሻያ ሃሳቦች ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች በማሳወቅ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ማመቻቸት ይጠበቅበታል፡፡

በመጨረሻም በኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት መረጃ የተሰበሰበባቸው የፌዴራል እና የክልል መ/ቤቶች እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

**አባሪ 1**

## <u>የኦዲት መመዘኛ መስፈርት</u>

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ | የኦዲት መስፈርቶች<br>EVALUATIVE CRITERIA |
|---|---|
| የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ስርዓተ-አስተዳደር መኖሩን፤ ተግባራዊ መደረጉንና ውጤታማ መሆኑን መገምገም | 1. በሀገሪቱ የሚገኙ የዱር እንስሳት ዓይነት፣ ብዛት፣ሥርጭት ሊጠና ይገባል፡፡ |
| | 2. በጥናቱ መሰረት የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች (የዱር እንስሳት ጥብቅ ክልል፤ የዱር እንስሳት መጠለያና የቁጥጥር አደን ቀበሌዎች) የሚቋቋሙባቸው ሥፍራዎች ሊለዩ ይገባል፡፡ |
| | 3. የሚቋቋሙት የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች በመገምገም የጥበቃ ቦታውን ዓይነት ለመወሰን የሚያስችል መስፈርት ሊኖር ይገባል፡፡ |
| | 4. በተዘጋጀው መስፈርት መሰረት የጥበቃ ቦታው አይነት ሊለይ ይገባል፡፡ |
| | 5. በጥናት የተለዩት የጥበቃ ቦታዎች ሊከለሉና ሕጋዊ ሰውነት ሊያገኙ ይገባል፡፡ |
| | 6. የሚቋቋሙት የጥበቃ ቦታዎች ዓለም አቀፍ ዕውቅና እንዲያገኙ ሊደርግ ይገባል፡፡ |
| | 7. በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የሚገኙ ወካይ ስነ-ምህዳር ያላቸውን ቦታዎች ከሰዎች ተፅዕኖ ለመጠበቅና በዘላቂነት ለማቆየት የሚያስችል የዞን ስርዓት (CONSERVATION ZONE/CZ/ AND CONSERVATION AND SUSTAINABLE NATURAL RESOURCE MANAGEMENT ZONE/C&SNRMZ/) ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 8. የጥበቃ ቦታዎች ሲቋቋሙ የማህበራዊ ምጣኔ ሃብት ጥናት(SOCIO ECONOMIC SUTDY) ሊካሄድ ይገባል፡፡ |
| | 9. በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የሚከናወኑ ሕገ-ወጥ ተግባራት (ሰፈራ፣የእርሻ ስራ፣ግጦሽ፣ወ.ዘ.ተ) ለመከላከል የሚያስችል የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 10. ለዱር እንስሳት ፓርኮችና መጠለያዎች ስርዓተ- አስተዳደር (PARK MANAGEMENT PLAN) ተዘጋጅቶላቸው ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 11. ስርዓተ- አስተዳደር(PARK MANAGEMENT PLAN) ሲዘጋጅ የአካባቢውን ህብረተሰብ ሊያሳትፍና ተጠቃሚነቱን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 12.በማንኛውም የዱር እንስሳት ጥበቃና መዘዋወርያ ቦታዎች ውስጥ የሚታቀድ የልማት እንቅስቃሴ ከመካሄዱ አስቀድሞ ጠቅላላ የማኔጅመንት እቅድ(GENERAL MANAGEMENT PLAN) የአካባቢ ተፅዕኖ ቅኝት(ENVIRONMENT IMPACT ASSESSMENT) የማኔጅመንት ዞን ዕቅድ(MANAGEMENT ZONE PLAN) ወይም የልማት ፅንሰ ሀሳብ እቅድ(DEVELOPMENT CONCEPT PLAN) አንፃር የፀደቀ ዝርዝር ማረጋገጫ ሊኖር ይገባል፡፡ |
| | 13. በፓርኮችና የዱር እንስሳት መጠለያዎች አካባቢ የሚከናወኑ ሌሎች የልማት እንቅስቃሴዎች የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት (IMPACT ASSESSMENT ) በቅድሚያ ሊሰራላቸው ይገባል፡ |
| | 14. በሀገራችን ብቻ የሚገኙ የዱር እንስሳት ዓይነት፤ ዝርያ ብዛት፤ ሥርጭትና የአኗኗር ሁኔታ ሊጠኑና በዘቦታዊ (ባሉበት ቦታ) ሊጠበቁ ይገባል፡፡ |
| | 15. በአልቂት ስጋት(ENDANGERD) ላይ ያሉ የዱር እንስሳት ዝርያዎች ጥበቃ እንዲደረግላቸው የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 16. ከዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች ውጭ ያሉት የዱር እንስሳትና የመኖሪያ አካባቢያቸው የሚተዳደሩበትና የሚጠበቁበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 17. በዱር እንስሳት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | 18. የዱር እንስሳትን ከተፈጥሮና ከሰው ሰራሽ አደጋዎች እንዲጠበቁ ለማድረግ የቅድመ-ማስጠንቀቂያ ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | 19. የቅድመ-ማስጠንቀቂያ ሥርዓቱም ሲዘረጋ የሚመለከታቸውን አካላት ያሳተፈ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 20. በሀገሪቱ ወካይ በሆኑ የጥበቃ ቦታዎች የተጠናከረ የዱር እንስሳት የሕክምና ጣቢያዎች ሊቋቋሙና አገልግሎት ሊሰጡ ይገባል፡፡ |
| | 21. ጉዳት የሚያደርሱ የዱር እንስሳት ዓይነትና የጥፋት መጠን ሊጠና ይገባል፡፡ |
| | 22. የዱር እንስሳቱም በሰው፤ በቤት እንስሳትና በሰብል ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ቅድመ-መከላከል ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 23. የበይና ተበይ (FOOD-CHAIN) ግንኙነቶችን በመከታተል የተፈጥሮ ሚዛን በማይናጋ ሁኔታ መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ |

| | |
|---|---|
| | 24. የዱር እንስሳቱን የመኖርያ አካባቢ የመሸከም አቅም (CARRYING CAPACITY) በየጊዜው ሊገመገም ይገባል፡፡ |
| የዱር እንስሳት ሀብት ላይ የተመሰረተ የቱሪዝም ልማት እንቅስቃሴዎች መኖራቸው፤ተግባራዊ መደረጋቸውንና ውጤታማ መሆናቸውን መገምገም | 25. የኢኮ-ቱሪዝም እንቅስቃሴ እንዲጎለብትና እንዲስፋፋ ዘላቂነት ያለው ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | 26. ኢኮ-ቱሪዝምን ለማጎልበትና ለማስፋፋት የሚያስችሉ የመሰረተ-ልማት አውታሮች ሊዘረጉ ይገባል፡፡ |
| | 27. የቱሪዝም እንቅስቃሴው በዱር እንስሳትና የመኖርያ አካባቢያቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳያሳድር ሕጎች፤ደንቦችና መመሪያዎች ተዘጋጅተው ተግባረዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡ |
| | 28. የጥበቃ ቦታዎች አካባቢን ተፈጥሮአዊ፤ ባህላዊና ታሪካዊ የቱሪዝም መስህብ የያዘ የቱሪስት ፓኬጅ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | 29. የቱሪስት ፓኬጁም ሲዘጋጅ ባለድርጃ አካላትን ባሳተፈ እና የቱሪስት ፍሰትን እና እንቅስቃሴን ሊገቱ የሚችሉ ባህላዊና አካባቢያዊ ተፅዕኖዎችን ማስወገድ በሚያስችል መልኩ መሆን አለበት፡፡ |
| | 30. የጥበቃ ቦታዎችን ማራኪ ገፅታ እና ለሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኙ የዱር እንስሳትና ውጤቶቻቸው በመገናኛ ብዙሃንና በመረጃ-መረብ የማስተዋወቅ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡ |
| | 31. ከዱር እንስሳት ጥናትና ከእያንዳንዱ የጥበቃ ቦታ (የዱር እንስሳት ዝርያ፤ አይነት፤ብዛት፤የመመገቢያ ሰዓት፤መራቢያ ወቅት ባህሪና የመሳሰሉት) የተገኙ መረጃዎች በመረጃ ማዕከል ተጠናቅሮ ሊያዝና ለተጠቃሚዎች ሊደርስ ይገባል፡፡ |
| | 32. ቱሪስቶች በፓርኮችና መጠለያዎች ውስጥ የተከለከሉ ተግባራትን እንዳይፈጽሙ ለማድረግ የሚያስችል የቱሪስት መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 33. የዱር እንስሳት አደን የሚካሄድባቸው ቦታዎችና ለአደን የሚውሉ እንስሳት ዓይነትና ብዛት ተለይተው ሊታወቁ ይገባል፡፡ |
| | 34. በቁጥጥር የአደን ቀበሌና ከጥበቃ ቦታዎች ውጪ ያሉትን የዱር እንስሳት ሥርጭት በማያዛባ መልኩ የአደን ኮታ ሊወጣና ለስፖርታዊ አደንና ሌሎች ጥቅሞች ሊውል ይገባል፡፡ |
| | 35. የዱር እንስሳት አደን በተመደበው ኮታ መሰረት ለመከናወኑ ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 36. የዱር እንስሳትና ውጤቶቻቸው ዝውውር አግባብ ባለው መንገድ እንዲካሄድ ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 37. የዱር እንስሳትና ውጤቶቻቸው ለንግድም ሆነ በሌላ ምክንያት ከአገር ውጪ ወይም በአገር ውስጥ በሚዘዋወሩበት ጊዜ አስፈላጊው የኳራንቲን ደንብ ማሟላታቸውን የሚረጋገጥበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 38. የዱር እንስሳት አጠማመድ ዓለም ዓቀፍ የእንስሳት ደህንነት መስፈርቶችን ያሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 39. በዱር እንስሳት መቆያ ስፍራ ዝግጅትና ዓለም ዓቀፍ የእንስሳት ደህንነት መስፈርቶችን ያሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 40. የግል ባለሀብቶች በዱር እንስሳት አስተዳደር፤ ጥበቃ፤ ልማትና አጠቃቀም እንዲሳተፉ ለማድረግ የሚያስችል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 41. በዱር እንስሳትና ውጤቶቻቸው ንግድ ላይ ለተሰማሩ ባለሀብቶች በዱር እንስሳት አጠቃቀም ደንብና መመሪያ መሰረት ፈቃድ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 42. ባለሀብቶቹም በደንቡና መመሪያው መሰረት ተግባራዊ ማድረጋቸው ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 43. ሕብረተሰቡ ከጥበቃ ቦታዎች ውጭ የዱር እንስሳት ቦታዎችን በባለቤትነት ይዞ በመጠበቅና በማልማት ተጠቃሚ የሚሆንበት ሁኔታ ተመቻችቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| በአገሪቱ ያለውን የዱር እንስሳት ክምችት(INVENTORY) ለማወቅ፤ ለመጠበቅና የዘለቄታዊ አጠቃቀም ስልት ለመቀየስ | 44. በሀገራችን የሚገኙ የዱር እንስሳት ዓይነት፤ዝርያ፤ብዛት፤ሥርጭትና የአኗኗር ሁኔታ መረጃ በማዕከል ደረጃ ሊያዝ ይገባል፡፡ |
| | 45. ቢያንስ በየአምስት አመቱ መረጃው ወቅታዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 46. የጥበቃ ቦታዎችን ማራኪ ገፅታ የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ በተጠቃሚዎች አይነትና ፍላጎት መሰረት ለእያንዳንዱ የጥበቃ ቦታ ተዘጋጅቶ በመረጃ ማዕከል ሊቀመጥ ይገባል፡፡ |
| | 47. በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥና በአካባቢው ለሚገኘው ሕብረተሰብ ስለ |

| | |
|---|---|
| **የሚረዳ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ መኖሩን፤ተግባራዊ መደረጉንና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ** | ጥበቃ ቦታው ሁለንተናዊ ጠቀሜታ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡ |
| | 48. የዱር እንስሳት ሊያደርሱ ስለሚችሉት ጥፋትና የመከላከያ ዘዴዎች እንዲሁም ጉዳት አድርሰው ሲገኙ መወሰድ ስለሚገባው እርምጃዎች ለህብረተሰቡ ትምህርት ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 49. ስለ ዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች አገልግሎት ከተጠቃሚዎች አስተያየት የሚሰበሰብበትና ተገምግሞ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል የመረጃ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 50. ከዱር እንስሳት ጥበቃና አጠቃቀም ጋር ተያያዥነት ያለው ስራዎችን ከሚሰሩ መንግስታዊ፤መንግስታዊ ከልሆኑ ድርጅቶችና ዓለምአቀፍ ተቋማት ጋር አስፈላጊ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 51. በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ ለሚከናወኑ የቱሪዝም እንቅስቃሴዎች የሚያግዙ መረጃዎች( የጥበቃ ቦታውን አጠቃላይ ገፅታ ገላጭ በራሪ ወረቀቶች፤አቅጣጫ ጠቋሚ ካርታዎች ወ.ዘ.ተ) ተዘጋጅተው ለተጠቃሚዎች ሊደርሱ ይገባል፡፡ |

አባሪ 2

## GLOSSARY

1. ENDEMIC SPECIES- በሀገራችን ብቻ የሚገኙ /ብርቅዬ/ የዱር እንስሳት
2. CITES-Convention international trade in dedanged species of wild faund and flor/አደጋ ላይ ያሉ እንስሳትና እፅዋት አለምዓቀፍ ንግድ ስምምነት
3. TRAFFIC-Trade records and analysis founal & flora in commerce- በዓለም አቀፍ ደረጃ ለንግድ የዋሉ የዱር እንስሳትና ዕፅዋት መረጃ የማሰባሰብና የመተንን ስራ የሚያከናውኑ ተቋም
4. ZOO- መዋዕለ እንሰሳት
5. SOCIO-economic survey- የማህበራዊ ምጣኔ ሀብት ጥናት
6. IUCN- አለምአቀፍ የተፈጥሮ ጥበቃ ህብረት
   Internationl union for conservation of nature
7. Transfer protected area- ድንበር ተሻጋሪ የሆነ የጥበቃ ቦታ
8. Endengeral species- በአልቂት ላይ ያሉ የዱር እንስሳት ዝርያዎች
9. Concession fee- የዱር እንስሳት የቁጥጥር አደን ቀበሌ አመታዊ የቦታ ኪራይ
10. Trophy size- የማርጣ መጠን
11. Ec-system- ስርዓተ ምህዳር
12. Ecological monitoring- ሰው ሰራሽ እና ተፈጥሮአዊ ለውጦች ክትትል
13. Consumptionve utilization- ፍጆታዊ የአጠቃቀም ስልት- የዱር እንስሳትን ወይም ውጤቶቻቸውን ከመኖሪያ አካባቢያቸው በመውሰድ ጥቅም እንዲሰጡ የሚደረግበት የአጠቃቀም ስልት
14. Non-consumptive utilization- ኢ-ፍጆታዊ የአጠቃቀም ስልት- የዱር እንስሳቱንም ሆነ ውጤቶቻቸውን ከመኖሪያ አካባቢያቸው ሳይወስድ ጥቅም እንዲሠጡ የሚደረግበት የአጠቃቀም ስልት
15. ታክሲ ደርሚ- የዱር እንስሳትን ህይወት ያላቸው አስመስሎ በቅርጻቸው መስራት
16. Environmental impact assessment- የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት
17. Management zone plan- የአስተዳደር ዞን ዕቅድ
18. Development concept plan- የልማት ፅንሰ ሀሳብ ዕቅድ
19. Park mnmagement plan- የጥበቃ ቦታ ስርዓተ-አስተዳደር ዕቅድ
20. Base line data- ለሚሰጡ ውሳኔዎች መነሻ መረጃ